EEA/EEPRI

Ethiopian Economic Association/ Ethiopian Economic
Policy Research Institute
Tel. 251-1- 55 74 59, 251-1 12 80 77
Fax No. 251-1 56 52 52
P.O.Box 34282, A.A Ethiopia:
e-mail: eea@telecom.net.et

EEA/EEPRI

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር/
የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ምርምር ተቋም

# የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ጽንሰ ሃሳብና አዘገጃጀት ሂደት

## ለድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ስልጠና የተዘጋጀ

አቶ ጌታሁን ታፈሰ እና አቶ ሰኢድ አሊ
መስከረም 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| እርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 1 |
| 1. የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ክስተት ምክንያቶች | 5 |
| 1.1 የድህነት ሁኔታ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች መባባስና መስፋፋት | 5 |
| 1.2 የአለም ባንክና የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የኢኮኖሚ ማስተካከያ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ውጤታማ አለመሆን | 7 |
| 1.3 የማያንሰራራ የዕዳ ጫና ውስጥ መዘፈቅ | 10 |
| 1.4 ሕዝባዊ ዓመጽ እና ግፊት በዕዳ ስረዛ ዙሪያ | 10 |
| 1.5 የድህነት ለማስወገድ መወሰድ ስላለባቸው ዕርምጃዎች የጋራ ግንዛቤ መዳበር | 11 |
| 2. ህዝቡ ድሀ ነው ሲባል ምንድነው መስፈርቱ? | 13 |
| 3. በሀገራችን የሕዝቡ ኑሮ ደረጃ የሚገኝበት ሁኔታ | 16 |
| 3.1 ድህነት የሰፈነባቸው ቦታዎች ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች | 18 |
| 4. የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዓላማ ይዘት እና አዘገጃጀት | 19 |
| 4.1 የድቅስ ሰነድ ዓላማ | 19 |
| 4.2 የድቅስ ሰነድ ይዘት | 20 |
| 5. የድቅስ ሰነድ ለኢትዮጵያ የሚኖረው ጠቀሜታ | 27 |
| 6. የድቅስ ሰነድ አዘገጃጀት ሂደት | 35 |
| ማመስከሪያ | 41 |

# የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብና አዘገጃጀት ሂደት

## መግቢያ

በዓለማችን የተለያዩ ሥልጣኔዎች በተለያየ ወቅት ተከስተው ብርሃናቸው ደምቆ ሲፈነጥቅ ቆይቶ እያደር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደበዘዙ በመጨረሻም ደብዛቸው ጠፍተው ቀርተዋል። በሌሎች አህጉሮች የግሪክ፣ የሮማውያን፣ ወዘተ ስልጣኔዎች በስፋት የሚታወቁ ሲሆን በአህጉራችን አፍሪካ በተለይ በግብፅ እና በኢትዮጵያ የነበሩ ስልጣኔዎች በአንድ ወቅት ከፍተኛ ደረጃ ይገኙ እንደነበር በታሪክ የተመዘገበና ከትውልድ ትውልድ በተላለፉ ቅርጾች የተረጋገጠ ሆኖ ይገኛል። በኢትዮጵያ የአክሱማይት ስልጣኔ ባለፈው ክፍለዘመን መጀመሪያ በአለም ላይ ከነበሩ አራት ዋና ዋና ስልጣኔዎች አንዱ እንደነበር በተለይ የሚታወቅ ነው። መሀከለኛ ክፍለ ዘመን (1315-1650) በሚባለው ወቅት ወደ አፍሪካ ከተለያዩ የአውሮፖ ሀገሮች እየመጡ ታሪክን ሲያጠኑ ከነበሩ ተመራማሪዎች መሃከል አልቫሬዝ፣ የተባሉት በወቅቱ በኢትዮጵያ የነበረው የእድገት ደረጃ በተለይም በማህበራዊ ኑሮና የግብርና ምርት አሠራርና ውጤት ኢትዮጵያ ከአውሮፖ በተሻለ ደረጃ ትገኝ እንደነበረ ዘግበዋል።

ይሁን እንጂ በመሀከለኛው ክፍለ-ዘመን ማብቂያ በእንግሊዝ ሀገር በተጀመረው የኢንዱስትሪ አብዮት በቅደሚያ በአውሮፖ በመቀጠልም በሌሎች አህጉሮች የሚገኙ ሀገሮች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከጊዜ ወደጊዜ ፈጣን እድገት እያገኙ ሲሄዱ በአፍሪካ የሚገኙ ሀገሮች ተመሳሳይ ቴክኖሎጂዎችን ባለመፍጠራቸው ወይም የሚታወቁ ቴክኖሎጂዎችን በመውሰድ ከኢኮኖሚያቸው ባለማዋሀዳቸው ይህ ነው የሚባል እድገት ሳያሳዩ ሕዝቦቻቸው በድህነት ኑሮ የሚማቅቁ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገሮች ኋላ ቀር የሚል ስያሜ አግኝተዋል።

በአውሮፖ የሚገኙ ሀገሮች ከእድገታቸው ፈጣንነት የተነሣ የጥሬ ዕቃና የሰው ጉልበት ፍላጉታቸው በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ እንዲሁም ሃያላን ሀገሮች እየሆኑ በመምጣታቸው ከ19ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ የአፍሪካ ሀገሮችን በቅኝ ግዛት በመያዝ ጥሬ ሀብታቸውን ከመመዝበራቸው በላይ በባርነት በመግዛት ጥንታዊ ባህላቸውንና የታሪካዊ የእድገት ጉዳናቸውን አጨናግፈዋል። ኢትዮጵያ ምንም እንኳ በዚህ የቅኝ ግዛት በቀጥታ ተጠቂ ባትሆንም እድገቷን የሚያስተጓጉሉና የሚያናጉ ልዩ ልዩ ተጽእኖዎች ተደርጉባታል።

## የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

ካለፈው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነታቸውን እያገኙ ወደ ፈጣን እድገት ለማምራት ጥረት ቢያደርጉም በአንደንድ መስኮች ካገኟቸው አዝጋሚ ለውጦች በስተቀር መሠረታዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የአኗኗር ለውጥ ማምጣት ሳይችሉ አሁንም በድኀነት ላይና ኋላቀር ሆነው ይገኛሉ:: ለዚህም ነው የአፍሪካ ሀገሮች ከፖለቲካ ቅኝ ግዛት ነፃ ቢወጡም አሁንም ድረስ በኢኮኖሚ ቅኝ ግዛት ስር ይገኛሉ የሚባለው::

በተለይም እ.ኤ.አ ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ በተከሰተው የአለም ነዳጅ ዋጋ ማሻቀብና ባደጉ ሀገሮች በተከሰተው የኢኮኖሚ ዝግመት ከአፍሪካ ሀገሮች የሚፈለጉ ጥሮ ዕቃዎች ዋጋና መጠን በማሽቆልቆሉ በአፍሪካ ሀገሮች የተጀመረው የእድገት ጥረት በከፈተኛ ደረጃ ሊስተጓጐል ችሏል:: በዚህ ወቅት የተከሰተው ችግር በኢትዮጵያም የዓፄው መንግስት እንዲወድቅ ከነበሩት ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል::

በአፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች የአብዛኛዎቹ ኢኮኖሚ በከፋ ሁኔታ በመጐዳቱ ካጋጠማቸው ቀውስ ለመውጣት የአደጉ ሀገሮችን እርዳታ ከምንጊዜውም በላይ ሽተዋል:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው የአለም ባንክ እና የአለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅት የተባሉ ተቋሞች ለተቸገሩ የአፍሪካ ሀገሮች ከፍተኛ ገንዘብ በብድር መልክ መስጠት የጀመሩት እነዚህ ተቋሞች አስቀድመው የተቋቋሙት በአለም ላይ የፋይናንስ ሁኔታን ለማረጋጋት ሲሆን ለአፍሪካ ሀገሮች ብድሩን ሊሰጡ ቅደመ-ግዴታዎችን እያስገቡ ነበር:: ተቋማቱ የሚያስቀምጧቸው ቅደመ-ሁኔታዎች ሀገሮች መውሰድ ያለባቸውን የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችንና ማራመድ የሚገባቸውን የኢኮኖሚ ሥርዓትና ፕሮግራሞች በተመለከተ ነው:: እነዚህም ባብዛኛው በነፃ የገበያ ሕግጋት፣ የዋጋ ግሽበትን በመከላከል የመንግሥት በጀት ጉድለትን በማጥፋት ላይ ያተኮሩ ነበሩ::

ይሁን እንጂ ባለፉት ሰስት አስርተ ዓመታት የአፍሪካ ሀገሮች ከአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ስምምነት በማድረግ ያራምዳቸው የነበሩ ፖሊሲዎች በተለይ ድህነትን በመቀነስ ረገድ ይህ ነው የሚባል የረባ ውጤት ሳያስገኙ ቀርተዋል:: እነዚህ ሀገሮች የተረፉቸው ነገር ቢኖር ከፍተኛ የእዳ ጫና ሆኗል:: በአንድ በኩል የድህነት ሁኔታ መባባስ በሌላ በኩል ያለባቸው የእዳ ጫና ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ ልማት ጥረት ማድረግ የማይችሉበት ደረጃ ስላደረሳቸው የእዳ ቅነሣ ጥያቄ ዋና የልማት ጥያቄ እየሆነ መጥቷል:: የታዳጊ ሀገሮች መንግሥታት ከሚያቀርቡት የእዳ ቅነሣ ጥያቄ በተጨማሪ በአደጉ ሀገሮች የሚገኙ ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ድሃ ሀገሮች ላይ ያለባቸው እዳ እንዲሰረዝ ወይም እንዲቀንስ በመንግሥቶቻቸውና በአለም አቀፉ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ጫና እያደረጉ መጡ::

በነዚህ ሁኔታዎች መነሻነት እ.ኤ.አ መስከረም ወር 1998 ዓ.ም ላይ የአለም ባንክና የአለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅት አመራር ቦርዶች በጋራ ባደረጉት ስብሰባ ለሀገሮች የእዳ ቅነሣ በተፋጠነ መልክ ተግባራዊ ለማድረግ እና ቀጣይ ደጓሚ ብድሮች ለመስጠት በቅድሚያ ሀገሮቹ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሰነድ (Poverty Reduction Strategy Paper) እንዲያዘጋጁ ወሰኑ:: ከዚህ ጊዜም በኋላ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በዕዳ የተዘፈቁ ሀገሮች እዳ ቅነሣ የሚደረግላቸውና ተጨማሪ ብድር ሊሰጣቸው የሚችለው ይህን ሰነድ ሲያዘጋጁ ብቻ እንደሆነ መመሪያ ወጣ:: ሰነዱም የሚዘጋጀው መንግሥት የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ ድህነት ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ በመቀየስ መሆኑ ይፋ ሆነ::

የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሰነድ ከዚህ ቀደም ከነበሩ አሠራሮች የተለየ የሚያደርገው ሰነዱ የሚዘጋጀው በሚመለከታቸው ሀገሮች ሆኖ ባለቤትነቱ የየሀገሮቹ መሆኑ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በንቃት የሚሳተፉበት መሆኑ፣ በዋናነት ድህነትን በረዥም ጊዜ ለማጥፋት ያተኮረ መሆኑ፣ ሰነዱ በውጤት ላይ ያተኮረና ለዚህም መከታተያ ተገቢ አመልካቾችን የሚይዝ መሆኑ ናቸው::

በዚህ መመሪያ ጽሁፍ የሰነዱ ዓመጣጥ፣ ዓላማ፣ አፈፃጸም በዝርዝር የተዳሰሱ ሲሆን የመመሪያው ዓላማ ሰነዱ በኢትዮጵያ በሚዘጋጅበት ወቅት ህብረተሰቡ ንቁ ተሳተፎ እንዲያደርግ መሠረታዊ ግንዛቤዎችን ለማስጨበጥ ነው::

## በዓለም ላይ የድህነት ሁኔታ ምን ይመስላል

አብዛኛው ሕዝባቸው ድሃ እንደሆነ የሚታወቁ አገሮች የሚገኙት በተለይ በአፍሪካ እና በደቡብ እስያ (ወይም South Asia) ክፍለ አህጉሮች እንደሆነ ይነገራል::
በአፍሪካ ስንል ደግሞ በተለይ ከሰሃራ በታች የሚገኙ ሀገሮች የሕዝቦቻቸው የኑሮ ደረጃ ከዓለም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይነገራል::

ይህ ማለት ግን የአደጉ ወይም የበለፀጉ በሚባሉ ሀገሮች ውስጥ ድህነት የለም ማለት አይደለም:: መጠኑ አይብዛ እንጂ በእነዚህም ሀገሮች ድህነት በተለይም ስራ አጥነት፣ የመኖሪያ ቤት እጦት የመሳሰሉ ችግሮች ይገኙባቸዋል::

## የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

ባለፋት አርባና ሃምሣ አመታት በዓለም ላይ በአጠቃላይ የሕዝብ የኑሮ ሁኔታ እየተሻሻለ እንደሄደ ይነገራል:: ከ1950 ዎቹ ዓመታት ወዲህ ለምሣሌ አጠቃላይ የምርት መጠን በየዓመቱ በአማካይ ሰስት በመቶ እያደገ መጥቷል:: ሆኖም ይህ እድገት የተገኘው ባብዛኛው ባደጉ ሀገሮች እና በምስራቅ እስያ በሚገኙ ታዳጊ ሀገሮች ነው:: እነዚህ ጥሩ እድገት ያስመዘገቡ ሀገሮች የሕዝብ ብዛት እድገታቸውም ተመጣጣኝ እና አነስተኛ እንደነበር ይታወቃል:: በሌላ በኩል በኢኮኖሚ እድገት ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሀገሮች ደግሞ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት እድገት ታይቶባቸዋል:: በዚህም ምክንያት ባደጉ ሀገሮች እና ወደኋላ በቀሩ ሀገሮች መካከል የሚገኘው የኑሮ ሁኔታ ልዩነት እየሰፋ ወይም እየተባባሰ ሄዷል::

ድሃ በሚባሉ ሀገሮች አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ እያሽቆለቆለ ቢመጣም በአንዳንድ የኑሮ ሁኔታ አመልካቾች የመሻሻል ሁኔታ ታይቷል:: በተለይም በጤና በኩል አማካይ የእድሜ ዘመን ለምሣሌ ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገሮች ከ1960 ዓ.ም ወዲህ ከ43 ወደ 52 ከፍ እንዳለ፣ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው የሚሞቱ የሕፃናት ቁጥርም 96 ከ1000 ወደ 82 ከ1000 ዝቅ እንዳለ ታውቋል::

ይሁን እንጂ ድህነት አሁንም ቢሆን የዓለማችን አስከፊ ገጽታ እና ትልቁ ፈታኝ ክስተት ሆኖ ይገኛል::

- ከአንድ ቢሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ ወይም አንድ ሶስተኛ የሚሆነው የታዳጊ ሀገሮች ሕዘብ በፍፁም ድህነት ውስጥ የሚገኝና የእለት ተእለት ኑሮውን ለማሟላት የሚፍጨረጨር ሕዝብ ሆኖ ይገኛል::

- በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ሕፃናት ትምህርት ላይ አይገኙም:: የዛኑ የሚያህል ሕዝብ ደግሞ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት አያገኝም፣ ንጽህናው በተሟላ አካባቢም አይኖርም:: በዚህም ምክንያት ለምሳሌ በየዓመቱ ከ3ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች በሳንባ ነቀርሳና በወባ በሽታ እንደሚሞቱ ይነገራል::

ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ድህነት በገጠ ሩ በሚኖረው ሕዝብ ላይ የከፋ እንደሆነ ይኸውም በገጠር ከሚኖረው ሕዝብ ግማሽ ያህሉ በፍፁም ድህነት ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን በከተማ ከሚኖረው ሕዝብ ደግሞ 20 በመቶው ብቻ በድህነት ውስጥ እንዳሉ ታውቋል::

- የገጠሩ ሕዝብ ባጠቃላይ በከተማ ከሚኖረው ሕዝብ ጋር ሲነፃፀር በተለይ የማህበራዊ አገልግሎቶችን የማግኘት እድሉ በጣም አነስተኛ ነው።

- በቅርብ ይፋ ሆኖ የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም የሰብዓዊ ልማት ሪፖርት እንዳመለከተው በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች የኢኮኖሚ እድገት እያሽቆለቆለ መምጣቱ እንዲሁም በበለፀጉ ሀገሮች እና በድሀ ሀገሮች መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መምጣቱ ታውቋል። በተለይም በኤድስ በሽታ መስፋፋት ምክንያት ከላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው 52 ደርሶ የነበረው አማካይ የዕድሜ ዘመን በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ አሽቆልቁሎ እንደወረደ ይታወቃል።

## 1. የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሰነድ ክስተት ምክንያቶች

ድህነትን ለመቀነስ የሚደረግ ጥረት አዲስ ክስተት አይደለም። በተለያዩ የአለም ክፍሎች በተለያዩ ወቅቶች በድህነት ላይ የተለያዩ ዘመቻዎች ተካሂደዋል። የአፍሪካን ብንወስድ ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ነፃ ከወጡ በኋላ በበርካታ ሀገሮች የተመሠረቱ መንግሥታት መሪዎች ድህነት፣ ድንቁርና በሽታ ዋና ጠላቶቻችንና በቅድሚያ ልናስወግዳቸው የሚገቡ ናቸው በማለት ለብዙ ዓመታት ተገቢ ናቸው ያሏቸውን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን/ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ አድርገዋል። ሆኖም ድቅስስ በአሁኑ ወቀት በብዙ ድሃ ሀገሮች ዋና የልማት አጀንዳ ከመሆኑና በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የመወያያ ርእስ ከመሆኑ በተጨማሪ የተለያዩ ግብረ ሀይሎች/ኮሚቴዎች ተቋቁመው ለሰነዱ ዝግጅት ልዩ ልዩ አውደጥናቶችና ስብሰባዎች በመካሄድ ላይ ይገኛሉ። ለዚህ ሰነድ ክስተት በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ ዋናዋናዎቹ እንደሚከተሉት ቀርበዋል።

### 1.1 የድህነት ሁኔታ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች መባባስና መስፋፋት

የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (UNDP) ዓመታዊ የሰብዓዊ ልማት ሪፖርት (Human Development Report) እንዲሁም በአለም ባንክ በየዓመቱ የሚወጣው የዓለም ዕድገት ሪፖርት (World Development Report) እንደሚያመለክቱት ከሰሃራ በረሃ በታች የሚገኙ የአፍሪካ ሀገሮች አሁን ያሉበት ሁኔታ ከ30 ዓመታት በፊት ደርሰውነት ከነበረው የዕድገት ደረጃ ያነሰ ሆኖ

እንደሚገኝ አረጋግጠዋል። በሌላ በኩል ባደጉ ሀገሮች በዚህ ወቅት ፈጣን ዕድገት ያስመዘገቡበት ወቅት ሲሆን ለዚህም ዋና ምክንያቶች በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ግኝት ፈጣን ዕድገትና የዓለም መዋሀድ ክስተት (Globalization) ሂደት ይገኙባቸዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂ የመረጃ ልውውጥ ቴክኖሎጂ፣ የስነ-ሕይወት ቴክኖሎጂ በአዳዲስ ግኝቶች ፈጣን እምረታ ያሳዩ ሲሆን ይህም የዓለምን ዕርስ በርስ ቁርኝት በማጠናከር የአደጉ ሀገሮች ኢኮኖሚ እንዲበለፅግ አድርገዋል። በዚህም ምክንያት ያለንበት ዘመን በዕውቀት የሚመራ የኢኮኖሚ ዘመን በመባል ይታወቃል። በብዙዎች ዘንድም ዓለም አሁን በደረሰችበት የዕውቀት ደረጃ ድኅነትን ከዓለም ገፅታ ላይ ለማጥፋት የሰው ልጅ ዓቅም ወይም ችሎታ እንዳለው ይታመታል።

በዓለም ላይ ፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት ቢታይም የተገኘው ሀብት ወይም ጥቅም ባብዛኛው ለአደጉ ሀገሮች ነው። ከዓለም ላይ ሀብታም በተባሉ 20 ዋና ሀገሮች ያለው አማካይ የገቢ መጠን ድሀ ከተባሉት 20 የመጨረሻ ሀገሮች ያለው አማካይ ገቢ ጋር ሲነጻጸር በ37 ዕጅ የሚበልጥ ሲሆን ይህም ልዩነት ባለፉት 40 ዓመታት በእጥፍ እንከጨመረ ታቅቋል። የሕፃናት ሞት መጠ ንን እንከምሳሌ ብንወስድ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ያለው የሞት መጠን ከአደጉ ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር በ15 ዕጅ የሚበልጥ ሆኖ ይገኛል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመስፋፋት ላይ ባለው የHIV / AIDS በሽታ ምክንያት በአህጉራችን የሚገኙ ድሃ ሀገሮች ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እንደተጎዳና ወደፊትም የሀገሮቹን ዕድገት የማጨናገፉና ይበልጥ ወደ ድኅነት ጎዳና ሊወስዳቸው የሚችል እንደሆነ ይታወቃል። ለምሳሌ፣ በቦትስዋናና ዚምባቡዌ ከሚገኙ ጎልማሳ ሕብረተሰቦች ውስጥ አንድ አራተኛው በዚህ በሽታ ቫየረስ የተያዙ መሆናቸው ያውቋል።

እ.ኤ.አ. ከ1987 እስከ 1998 ባለው የቅርብ ጊዜ እንኳ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች በድኅነት የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር ከ217 ሚሊዮን ወደ 291 ሚሊዮን ከፍ ብሳል በሌላ በኩል እነዚህ ሀገሮች በዕዳ ጫና ውስጥ በመዘፈቃቸው ብዙ ሀገሮች እስከ አንድ አምስተኛ የሚሆነውን ዓመታዊ በጀታቸውን ለዕዳ ክፍያ ለማዋል ተገደዋል። በበርካታ ሀገሮች የሚገኙ መንግሥታትም ለማኅበራዊ አገልግሎቶች ከሚያውሉት ባጀት በላይ ለዕዳ ክፍያ እንደሚውሉ ታውቋል።

## 1.2 የአለም ባንክና የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የኢኮኖሚ ማስተካከያ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ውጤታማ አለመሆን

ከላይ እንደተጠቀሰው በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች የድህነት ሁኔታ እየተባባሰ የሄደው እነዚህ ሀገሮች ከአለም ባንክና ከአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ከፍተኛ ብድር እየወሰዱ በነዚህ ተቋማት የተዘጋጁ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት ነው:: የአፍሪካ ሀገሮች እ.ኤ.አ ከ1970ዎቹ ዓመታት ጀምሮ የኢኮኖሚ ማሽበት ሲያጋጥማቸውና ከፍተኛ ችግር ላይ በወደቁበት ወቅት አለም አቀፍ ተቋማቱ ከፍተኛ ገንዘብ ይዘው በመምጣት እነዚህ ሀገሮች ተመሳሳይ የሆኑ የኢኮሚኖሚ ማስተካከያ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ እንዳያደርጉ ጫና አድርገውባቸዋል::በአለም ባንክ እና የአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት የተዘጋጁና በተግባር እንዲውሉ የሚበረታቱ የኢኮኖሚ ማስተካከያና ማሻሻያ ፕሮግራመችና ይዘት ለማወቅ በቅድሚያ ተቋማቱ የተመሠረቱበት ምክንያቶችና ዓላማ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል::

የአለም ባንክና የአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት በመባል የሚታወቁት እህትማማች ድርጅቶች የተቋቋሙት Bretton Woods New Hampshire በሚባል ቦታ እ.ኤ.አ በ1945 ዓ.ም ነው:: በዚህም ምክንያት እነዚህ ድርጅቶች የብሬተን ውድ ተቋሞች በመባልም ይታወቃሉ::

እ.ኤ.አ በ1930 ዎቹ ዓመታት በአውሮፖ የሚገኙ ሀገሮች ኢኮኖሚ በከፍተኛ ዝግመት ውስጥ ገብቶ በመቀጠልም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሳቢያ ኢኮኖሚያቸው ክፉኛ የተጐዳበት ወቅት ነበር:: ሀገሮች በኢኮኖሚ ዝግመት ውስጥ ሲገቡ ኢኮኖሚውእንዲያንሰራራ መንግሥት ከፍተኛ ሚና እንዳለው በመታወቁ በጦርነት የተጐዱ ሀገሮች ኢኮኖሚን ለማንሰራራት በየሀገሮቹ ያሉመንግሥታት መጠናከርና ለዚህም ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው በመታወቁ የአለም ባንክ የተባለው ድርጅት እንዲቋቋም ሲደረግ ዓላማውም በጦርነት ደቆ የነበረውን የአውሮፖ ኢኮኖሚ ለመገንባት ነበር:: የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ወይም IMF የተባለው በተጓዳኝ የተቋቋመበት ዓላማዎችም አለም አቀፉ የገንዘብ ግንኙነቶች በትብብር ላይ የተመሠረቱ እንዲሆን ለማድረግ፣ ዓለም አቀፍ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲዳብር ለማድረግና የውጭ ምንዛሬ ገበያ የተረጋጋ እንዲሆን ለማድረግ ነበር::

እነዚህ አለም አቀፍ ተቋሞች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች እያራመዱ ባገኙት ልምድና ባላቸው የካፒታል መጠን እየተጠናከሩ ሲሄዱ አድማሳቸውን እያስፋሄደዋል:: እ.ኤ.አ በ1973 ዶንዳጅ

## የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

አምራች ሀገሮች የጋራ ድርጅት መመሥረትን አስከትሎ የነዳጅ ዋጋ በአንድ ጊዜ በማሻቀቡ በዓለም ላይ ባደጉ ሀገሮች የኢኮኖሚ ዝግመት ተከስቶ ይህም የታዳጊ ሀገሮችን ኢኮኖሚ ክፉኛ ጉድሟቷል:: (በሀገራችን ለዓፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት መወደቅ ከነበሩ ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ ይህ አንደኛው ነበር) በዚህም ወቅት ነበር የአለም ባንክና የአለም አቀፉ ገንዘብ ድርጅት ፊታቸውን ወደ አፍሪካ በማዞር ከፍተኛ ገንዘብ ለየሀገሮች በብድር መልክ መስጠት የጀመሩት ብድሩንም በሚሰጡ ጊዜራሳቸው የሚቀርጿቸውን ፖሊሲዎች እነዚህ የተቸገሩ ታዳጊ ሀገሮች ተግባረዊ እንዲያረጉ ጫና ማድረግ ጀመሩ:: በተለይም የዓለም ባንክ የተባለው ድርጅት የታዳጊ ሀገሮች የልማት ፕሮጀክቶች ዋና ፋይናንስ አየሆነ በመምጣቱ በአሁኑ ወቅት ታዳጊ ሀገሮች በጠቅላላው 160 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እዳ ከባንኩ ወስደው ለባንኩ ከፍተኛ ባለእዳ ሆነዋል::

በዚህ ምክንያት የእነዚህ ተቋሞች መሠረታዊ ዓላማ በአለም ላይ በነፃ ገበያ ህግጋት የሚመራና በውድድር ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ሥርዓት ማስፈን ነው:: በአፍሪካ የሚገኙ ድሃ ሀገሮች በአለም የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ተዋህደው ውድድሩን የመቋቋም ሀይል ይኑራቸው አይኑራቸው ለተቋሞቹ ዋና አሳሳቢ ጉዳይ ሊሆን አይችልም:: ተቋሞቹ የሚያራምዷቸው ፖሊሲዎች የተሠረቱባቸው የኢኮኖሚ ንድፈ ሃሣቦችና ሞዴሎች ባደጉ ሀገሮችን የኢኮኖሚ ሂደቶችና ግንኙነቶች ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው ለታዳጊ ሀገሮች ተገቢ ሊሆኑ እንደማይችሉ ቢታወቅም እነዚህ ተቋሞችን የሚያሳስብ ጉዳይ አልነበረም::

በተለይ እ.ኢ.አ በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች በተግባር እንዲያወሉ ግፊት የተደረገባቸው የመዋቅር ማሻሻያና የኢኮኖሚ ማስተካከያ ፕሮግራሞች (Structural reform and adjustment programs) ዋና ትኩረታቸው የኢኮኖሚ መረጋጋትን ለማምጣት እንደነበረ ቢነገርም ፕሮግራሞቹን ተግባራዊ ባደረጉ ሀገሮች በርካታ ማህበራዊ ቀውሶች ተከስተዋል:: በአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በግፊት ተግባራዊ የሚሆኑ ፕሮግራሞች የተመሠረቱባቸው የኢኮኖሚ ፖሊስ መርህዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

- በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግሥትን ሚና መገደብ/መቀነስ
- የመንግሥት የበጀት ጉድለትን ማጥፋት
- የዋጋ ንረትን ማጥፋት
- የወለድ ተመንን ማሳደግ
- የገበያ ቁጥጥርን ማጥፋት
- ነፃ ገበያ ማስፋፋት
- የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚን ማዳበር

ከላይ የተጠቀሱት መርሀዎች ለአንድ ኢኮኖሚው በከፍኛ እድገት ላይ ለሚገኝ ሀገር ተስማሚ ሊሆኑ ቢችሉም ለአንድ ታዳጊ ሀገር ኢኮኖሚ ማንሰራራትና ማደግ ግን አስፈላጊነታቸው አጠያያቂ ነው።

ለምሳሌ በታሪክ እንደታየው የተለያዩ መንግሥታት የሀገሮቻቸውን ኢኮኖሚ በማጎልበት ሰፊ ሚና ተጫወተዋል። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ ሀገሮች የገበያ ሥርዓት በሚገባ ባልዳበረበት የመንፍስትን ሚና መገደብ ወይም መቀነስ ዕርምጃ ጠቃሚነቱ አጠያያቂ ነው። በተጨማሪም የዛሬ ታላቋ  ሀገር አሜሪካ በቀድሞ የእድገት ታሪኳ መንግስት የበጀት ጉድለትን (Deficet Financing) በመጠቀም ሀገሬቷን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወቱ እና ተመሳሳይ ፖሊሲም ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ማብቂያ ማግስት ጀምሮ በአውሮፓ ሐገሮች የማርሻል እቅድ ተብሎ በሚታወቀው ፕሮግራም አማካኝነት ተግባራዊ ሆና ሀገሮቹ ከጦርነት ውድቀት እንዲያገግሙና ፈጣን እድገት እንዲያስገኙ ያስቻለ መሆኑ ይታወቃል።

በተለይም ታዳጊ አገሮች የመንግስት ጉድለትን ለማጥፋት በሚያደርጉት ሙከራ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንደ ትምህርት ጤና በመሳሰሉት ይመድቡ የነበረውን በጀት በመቀነሳቸው የትምህርት ሽፋን መቀነስ የበሽታ መስፋፋት በእነዚህም ምክንያት የድህነት መጨን መጨመር ሁኔታዎች ተከስተዋል። በአንዳንድ ሀገሮች በተፈጠረው ከፍተኛ የማህበራዊ ቀውሶች ለምሳሌ በብራዚልን በጋና ሕዝባዊ አመፆች ሊነሱ ችለዋል።

የማህበራዊ ውድቀት እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ ዓመታት እየተባባሰ በመሄዱ እ.ኤ.አ. በ1987 በተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መረጃ ድርጅት (UNICEF) አነሳሽነት "Adjestment with Human Face" ወይም ሰብዓዊ የሆነ የኢኮኖሚ ማስተካከያ እርምጃ እንዲመጣ ግፊት በመደረጉ በተለይ በ1990ዎቹ ያለፉ አስር አመታት በዓለም ባንክና በአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ፋይናንስ የሚደረጉ ፕሮችራሞች ለድህነት ሁኔታ ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ጥረት ተጀምሯል። ሀገራችን ኢትዮጵያዊም ከነዚህ ተቋሞች ጋር ስምምነት በማድረግና ብድር በመመስድ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ የጀመረችው በዚህ ወቅት በመሆኑ ለመህበራዊ ጉዳዮችና ለድህነት ቅነሳ ትኩረት የሚሰጡት የተሻሻሉ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ብታደርግም በሌሎች ሀገሮች እንድታየው ሁሉ ድህነትን በመቀነስ ረገድ ይህ ነው። የሚባል ውጤት አልተገኘም የዚህም ዋና ምክንያት በአለም አቀፍ ተቋሞች የተደረገው ማሻሻያ ከዓላማ ለውጥ ወይም ከልቡ የመነጨ ሳይሆን ለደህነት ቅነሳ ተሰጥቶ የነበረው ትኩረት በተቀጽላ የተደረገ ስር መሰረት የሌላው በመሆኑ ነው።

## 1.3 የማያንሰራራ የዕዳ ጫና ውስጥ መዘፈቅ

ከአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ብድር በመውሰድ የልማት ጥረት ያደርጉ የአፍሪካ ሀገሮች በስተመጨረሻው የተረፋቸው ከፍተኛ የዕዳ ጫና ነው። ኢትዮጵያ ጨምሮ በእነዚህ ሀገሮች ላይ የተከማቸው ዕዳ ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴ ማድረግ የማይችሉበት ደረጃ እንዲደርሱ አድርጓቸዋል። ሀገሮች ከዕዳ ጫና በዘላቂነት መላቀቅ መቻል አለመቻላቸውን የሚያረጋግጡ መለኪያዎች ተበጅተው ከፍተኛ ዕዳ ውስጥ የተዘፈቁ ድሃ ሀገሮችን ለመለየት ተችሏል። ኢትዮፐያም ባለበት ከፍተኛ የዕዳ መጠን ከነዚህ ሀገሮች ጎራ ልትመደብ ችላለች።

| የኢትዮጵያ የዕዳ መጠን እ.ኤ.አ. በ1988 ዓ.ም. | በሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር |
|---|---|
| አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት መጠን | 9,509.50 |
| አጠቃላይ ገቢ ከወጪ ንግድ | 1,629.90 |
| ጠቅላላ የዕዳ ከወጪ ንግድ | 7,486.60 |
| ዓመታዊ የዕዳ ክፍያ መጠን | 241.70 |
| ዓመታዊ የዕዳ ክፍያ ከወጪ ንግድ ገቢ ጋር ሲነፃፀር | 16 በመቶ |

ከላይ እንደተመለከተው ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቅነሳ ካልተደረገላት በሚፈጠርባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ኢኮኖሚዋ ሊያንሰራራ እና ትርጉም ያለው ዕድገት ልታመጣ እንደማትችል የተረጋገጠ ሆኗል። በተመሳሳይ መልኩ ብዛት ያላቸው የአፍሪካ ሀገሮች ከወጪ ንግድ የሚያገኙት ገቢ ከፍተኛ ድርሻ ያለውን መልሰ ለወለድና ዕዳ ክፍያ ስለሚያውሉት ከውጭ መሰረታዊ የሆኑ እንደመድሃኒትና ነዳጅ የመሳሰሉ ፍጆታዎታቸውን ለማግኘት ስላዳገታቸው አስፈላጊ የካፒታል ዕቃዎችን ወደ ሀገራቸው በማስገባት ልማት የሚያራምዱበት ተስፋ እየመነመነ መጥቷል።

## 1.4 ሕዝባዊ ዓመፅ እና ግፊት በዕዳ ስረዛ ዙሪያ

ድሃ የሆኑ ታዳጊ ሀገሮች ያለባቸው ዕዳ እንዲሰረዝ / እንዲቀነስ የሀገሮቹ መንግሥታት ከሚያቀርቡት ጥያቄ፣ የተለያዩ የኃብረተሰብ ክፍሎችና መንግታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያደረጉት የተቀናጀ እንቅስቃሴ ይበልጥ ውጤታማ እየሆነ መጥቷል። የአፍሪካ ሀገሮች መንግሥታት መሪዎች የተለያዩ የስብሰባ ውሳኔዎች ሀገሮቻቸው ያለባቸው ዕዳ እንዲሰረዝ በተለይ ወቅት ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ጥያቄው ጆሮ ዳባ ለብሰ ተገቢው ምላሽ ሳያገኝ ቆይቷል። መንግስታዊ ያልሆኑ የረድዔት ድርጅቶች ከእነዚህ ሀገሮች ጎን በመቆም ተመሳሳይ ጥያቄ ሲያቀርቡ የቆዩ ሲሆን ይህም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባደጉ ሀገሮች በሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እያገኘ

በመንግስታቸው ላይ ተቃውሞ በማንሳትና በአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ላይ የሚያደርጉት ግፊት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ PRSP ወይም የድኅነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ጽንሰ ሃሳብ እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል:: በዕዳ ስረዛ/ቅነሳ ዙሪያ የተካሄዱ ጠንካራ እንቅስቃሴዎች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ::

## 1.5 የድኅነትን ለማስወገድ መወሰድ ስላለባቸው ዕርምጃዎች የጋራ ግንዛቤ መዳበር

ድኅነት በአለማችን ላይ የሚገኝ አስከፊ ገፅታ ከመሆኑ በላይ ችግሩ በአንድ ክልል ተወስኖ የማይቀርና ለሌላውም የሚተርፍ መሆኑ በተጨማሪም አለም አሁን በደረሰችበት የቴክኖሎጂ የዕድገት ደረጃ ይህን ችግር ከምድር ገፅ ለማጥፋት የሚያስችል ሀብትና ዕውቀት እንዳላት ያለው የጋራ ግንዛቤ እያደገ መጥቷል:: የለም በሰልጣኔ እየበለፀገች የሰው ልጅ የተሟላ ሰብዓዊ መብቶች መከበርና የአካባቢ ብክለትን መቆጣጠር ዋና የዕድገት ዓላማዎች እየሆኑ በመጡበት ወቅት በድኅነት የሚማቅቁ ሕዝቦች መኖር የተጠቀሱትን ቅዱስ አለማዎች ለመተግበር ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል:: የሰብዓዊ መብት ጥያቄም ከፖለቲካ አድማስ በመሻገር የትምህርት ዕድል፣ የጤንነት የመሟላት ወዘተ በአጠቃላይ ከድኅነት የመላቀቅና የኢኮኖሚ ነፃነት ጥያቄ እየሆነ መጥቷል:: በተመሳሳይ መልኩ የአካባቢ ብክለት መወገድ ከድኅነት መወገድ ጋረ ተደጋፊና የተቆራኘ መሆኑ ይበልጥ ሊታወቅ ችሏል::

በሌላ በኩል ከዚህ ቀደም ድኅነትን ለመቀነስ የተጠነሰሱ ፖሊሲዎችና የተዘረጉ ፕሮግራሞች ውጠ.ታማ ሊሆኑ ታስቻሉበት ምክንያቶች ይበልጥ ግልፅ እየሆኑና በስፋት እየታወቁ መጥተዋል:: ለድህነት መወገድ እንቅፋት እንደሆኑ ወይም ድህነትን እንደ ሚያባብሱ ከታወቁ ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

ጠቅለል ባለመልክ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል ባለፉት ሃያ አመታት በአብዛኛው የአፍሪካ ሃገሮች የህዝቡ የኑሮ ሁኔታ እንዳይሻሻል እንቅፋት ከነበሩ ምክንያቶች ውስጥ፡-

1. ሀገሮች ትክክለኛ የልማት ፖሊሲና ስልት በተግባር አለመቀላቸው ዋነኛው ምክንያት ሲሆብ ይህም የኢኮኖሚ እድገታቸው በአብዛኛው እየቀነሰ እንዲመጣ አድርጓል:: መጠነኛ የኢኮኖሚ እድገት ባሳዩ ጥቂት አገሮችም ቢሆን የሀብት ክፍፍሉ የተዛባ በመሆኑ የድህነት ሁኔታ የተባባሰ እንጂ የተሻለ አልሆነም::

2. በእነዚህ አገሮች እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የዲሞክራሲ አሰራር ያልሰፈነ ስለነበረና በአንባገነንነት ያስተዳድሩ የነበሩ መንግስታት ለህዝቦቻቸው ኑሮ መሻሻል የነበራቸው ኃላፊነት ደካማ መሆኑ ሌላው እንቅፋት ነበር:: በተለይም ጥሩ አስተዳደት (Good Governance) አለመኖር::

3. በነዚህ መንግስታት የነበሩ ኢኮኖሚዎች መዋቅሮቻቸው የተዛባ መሆኑ: ለምሳሌ የመንግስት ወጪ በተንዛዛ የቢሮክራሲ አሰራር ላይ የሚባክን በመሆኑ መሰረታዊ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተቋሞች ሊስፋፉ ባለመቻላቸው:
   - የመንግስት ወጪ ከገቢው ብዙውን ጊዜ ከገቢው ስለሚበልጥ የበጀት ጉድለት መፈጠሩና ይህም የዋጋ ግሽፈት የሚያስከትል መሆኑ
   - የእነዚህ ሀገሮች የውጭ ንግድ በጥሬ ዕቃ ላይ በመመስረቱ እና የገቢ ንግዱ ከፍተኛ ሆኖ አለመመጣጠኑ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የሚያስከትልና የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚን የሚያደክም መሆኑ ናቸው::

4. ሌላው ዋነኛ እንቅፋት ሆኖ የቆየውና አሁንም ቢሆን በአንዳንድ አገሮች ለኢኮኖሚያቸው ድቀት ምክንያት በመሆን ላይ የሚገኘው በሀገሮች ውስጥ ሰላምና መረጋጋት አለመኖር ነው::

እነዚህ እስካሁን የጠቀስኳቸው ነጥቦች አጠቃላይ በሀገር ደረጃ የሚከሰቱ ችግሮች ሆነው የህዝቡ ኑሮ እንዲያሽቆለቁል የሚያደርጉ ሲሆን ይህም የሚሆነው በተለያየ መንገድ ነው:: ወይም በሌላ አነጋገር በህዝቡ ደረጃ ድህነትን የሚያመጡ ምክንያቶች ውስጥ:

1. ስራ የማግኘት ዕድል ጠባብ መሆን
2. በቂ እሴት ለምሳሌ መሬት ወይም ካፒታል ማግኘት አለመቻል
3. ድሃው ህብረተሰብ ሊሸጥ ለሚችላቸው አቅርቦቶች አመቺ የገበያ ሁኔታ አለመኖር
4. በቂ ማህበራዊ አገልግሎቶች በተለይም ትምህርት፣ ጤና፣ ንጹህ ውሃ ማግኘት አለመቻል
5. የተፈጥሮ ሃብቶች እየተራቆቱ መሄድ
6. ህብረተሰቡ በልማት ፕሮግራም ዲዛይኖች ላይ የመሳተፍ አቅሙ ውሱን መሆኑ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው::

ለማጠቃለል ድህነትን በተሳካ ሁኔታ ማስወገድ የሚቻለው:

- ህዝቡ የተሳተፈበትና በጋራ ግንዛቤ ያመነባቸው ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በስራ ሲውሉ፣
- የመንግስት አሰራር ግልፅነት ያለውና በተዋረድ ተጠያቂነት ያለበት ሲሆን፣
- የድህነት ችግሮች ተጠንተውና አንገብጋቢ የሆኑት በቅደም ተከተል ተለይተው በነዚህ ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች በተግባር ሲውሉ፣
- የተቀናጀና የተደጋገፈ ሁሉንም ክፍለ ኢኮኖሚዎችን የሚያካትት ፕሮግራም በተግባር ሲውል፣
- ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በጋራ በስራ የሚያውሉት የልማት ፕሮግራም ሲሆን

## 2. ህዝቡ ድህ ነው ሲባል ምንድነው መስፈርቱ?

- ድህነት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በሁለት መንገድ ይተረጎማል

- አንድኛዉ ፍጹም ድህነት ወይም (Absolute Poverty) የሚባለው ሲሆን ይህም አንድ ቤተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶት ለማሟላት የሚያችለውን ዝቅተኛውን አስፈላጊ የኑሮ ደረጃ የሚለካ ነው:: በዚህ አተረጓጎም እንግዲህ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላሟሉ ቤተሰቦች ድሃ ይባላሉ ማለት ነው:: እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች የሚያካትቱት በቂና ተመጣጣኝ ምግብ፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ ንጽህናው የተሟላ መጠለያ፣ ልብስ እና በተጨማሪም መሰረታዊ የጤና እና የትምህርት አገልግሎት የማግኘት ዕድል ናቸው::

- ሁለተኛው ድህነት የሚተረጎምበት መንገድ ደግሞ አንጻራዊ ድህነት ወይም (Relative poverty) የሚበለው ነው:: ይህም አንዱን ቤተሰብ ከሌላው ቤተሰብ አንዱን ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ እያወዳደረ የኑሮ ደረጃ ልዩነትን የሚለካ ነው:: በዚህም ምክንያት አንጻራዊ ድህነት በሀብት ክፍፍል ረገድ ባለው እና በቤተሰብ የገቢ መጠን ባለው ልዩነት ላይ የሚያተኩር ነው:: በዚህ አተረጓጎም መሰረት እንግዲህ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የቻሉ ቤተሰቦች እንኳ ከሌላው በከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ቤተሰቦች ጋር እየተነጻጸሩ ድሃ ሊባሉ የሚቻልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ማለት ነው::

- ባዚህም ነው አንጻራዊ ድህነት ባብዛኛው የአደጉ ወይም የበለጸጉ አገሮች ችግር ተደርጎ የሚወሰደው

- እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉ በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገሮች አንገብጋቢ ችግራቸውና ቀዳሚውን ትኩረት ሊወስድ የሚገባው እንግዲህ ፍፁም ድህነትን መቀነስ ወይም ማጥፋት ላይ መሆን አለበት ማለት ነው::

- ድህነት እንግዲህ በኑሮ ደረጃ የሚተረጎም ከሆነ የድህነት መለኪያ ማለት የኑሮ ደረጃ መለኪያ ይሆናል ማለት ነው:: የኑሮ ደረጃን ለመለካት እስካሁን በስፋት በስራ ላይ የዋሉ መለኪያዎች ደግሞ የቤተሰብ የነፍስ ወከፍ ገቢ እና የነፍስ ወከፍ ወጪ ናቸው:: ይህ የነፍስ ወከፍ ገቢ ወይም ወጪ የሚሰላው ደግሞ አማካኝ የቤተሰብን ገቢን ወይም ወጪን (የወር ወይም የአመት ሊሆን ይችላል) በቤተሰቡ የሰው ብዛት መጠን በማካፈል የሚገኝ ነው::

  የነፍስ ወከፍ ገቢ ወይም ወጪ መጠን እንግዲህ ለአንድ ሰው የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት በቂ ሆኖ ካልተገኘ በዛቤተሰብ የሚገኙ ሰዎች በፍፁም ድህነት ውስጥ ነው ማለት ይሆናል::

- ለዚህም ነው ለበርካታ አመታት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ የሀገሮች የእድገት መለኪያ እና ማወዳደሪያ ሆኖ ሲወሰድ የቆየው::

- በእርግጥ የነፍስ ወከፍ ገቢ ወይም ወጪ በገንዘብ የሚሳለና ሌሎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለምሳሌ የተሟላ ጤንነትን፣ ትምህርት የማግኘት ዕድልን፣ ንፁህ ውሃ፣ መንገድ የመሳሰሉ የህዝብ መገልገያዎችን (Public Goods) የማግኘት ዕድልን በሚገባ የሚያንጸባርቅ አይደለም::

- በተለይም በቅርብ ጊዜ ወዲህ ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት የልማት ትርጉም እራሱ በኢኮኖሚ ወይም በገቢ እድገት ብቻ መተርጎሙ ቀርቶ ልማት ማለት የሰዎች አጠቃላይ ሰብዓዊ ደህንነት መሻሻል ነው የሚለው ግንዛቤ ይበልጥ ተቀባይነትን በማግኘቱ: የሃገሮች ዕድገት መለኪያ የህዝቦቻቸው አጠቃላይ የሰብዓዊ ደህንነት ሁኔታ እየሆነ በመምጣቱ የድህነት መለኪያም የነፍስ ወከፍ ገቢ ወይም ወጪ ብቻ ሳይወሰን እያንዳንዱ ቤተሰብ በተለይ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች የማግኘት እድሉን የሚያካትት ይሆናል::

በዚህም መሰረት

- መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚያስችለው የገቢ መጠን ሲሰላ ለምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ ከሚያስፈልገው ወጪ በተጨማሪ መሰረታዊ ትምህርት እና ጤና አገልግሎቶች ለማግኘት የሚያስፈልገው ወጪ ተካቶ የሚሰላ ይሆናል።

- በዚህም መልክ የሚሰላውና ዝቅተኛውን የተሟላ የሰብዓዊ ደህንነት ሁኔታ ለመኖር የሚያስችለው የገቢ መጠን የድህነት ገደብ መስመር ወይም (Poverty Line) የሚባል ሲሆን የገቢ መጠናቸው ከዚህ ገደብ በታች የሆኑ ሁሉ በድህነት ይወጠራሉ ማለቱ ነው።

- ይህ የድህነት ገደብ መጠን ከሃገር ሀገር ከቦታ ወደ ቦታ የሚለያይ ሲሆን የሚወሰነውም በአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ነው።

የአለም ባንክ የታዳጊ ሃገሮችን የልማት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ፋይናንስ የሚያደርግ ድርጅት ሲሆን ድርጅቱ ባወጣው ስሌት መሰረት በዝቅተኛ የሚገኙ ሀገሮች የድህነት ገደብ ከ275 - 370 የአሜሪካን ዶላር የነፍስ ወከፍ አመታዊ ገቢ ሊወሰድ እንደሚችል ተቀምጧል። ይህንን ዝቅተኛውን ወስደን ወደ ሀገራችን ብንተረጉመው ምን ማለት ነው። በአማካኝ የወር ገቢያቸው ከ1440 ብር በታች የሆኑ ሰዎች በፍጹም ድህነት ውስጥ ይገኛሉ ማለቱ ነው። ነገር ግን ይህ ይከከለኛው የሀገራችን የድህነት ገደብ መለኪያ ነው ማለት አይቻልም። ለሀገራችን የሚሆን የድህነት ገደብ መለኪያ ለማውጣት መንግስት በአሁኑ ወቅት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ለዚህ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ የሀገር አቀፍ ደረጃ የቤተሰብ የመስክ ጥናት ወይም (National Household Survey) በማካሄድ በቤተሰብ ደረጃ የገቢና ፍጆታ መጠን፡ ሌሎች የማህበራዊ አገልግሎት አጠቃቀምን፣ የዋጋ ሁኔታን በተመለከተ መረጃ የሚያስፈልግ ሲሆን ይህ ጥናት ባሁኑ ግዜ ተጠናቆ የጥናቱ ውጤት በቅርቡ ይፋ እንደሚሆን ይጠበቃል።

ወደፊት በዚህ መረጃ ላይ በመመስረት አስፈላጊ ዝርዝር ጥናቶች ተካሂደው ትክክለኛው የሀገራችን የድህነት ገደብ መስመር የሚዘጋጅና የድህነት ሁኔታውን ለመከታተል ለዕቅድ ዝግጅት ለመሳሰሉ ስራዎች የሚውል ይሆናል።

## 3. በሀገራችን የሕዝቡ ኑሮ ደረጃ የሚገኝበት ሁኔታ

- እንደሚያወቀው አገራችን በአለም የመጨረሻ ኃላ ቀር ከሚባሉ ሀገሮች ስትመደብ የቆየች ናት:: በገሀድ እንደሚያወቀውም እስካሁን ድረስ በምግብ እንኳ ራሳችንን መመገብ የማንችልና በተለይም ድርቅ በተፈጠረ ግዜ ሁሉ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ህዝባችን በረሀብ አለንጋ እየተቀጠፈ ያልቅ እንደነበር የሩቅ ሳይሆን የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

  በሀገራችን ድህነት በገሃድ ተንሰራፍቶ የሚገኝ መሆኑን የሚያጠራጥር ነገር ያለ አይመስለኝም:: ድህነታችንንም ለማወቅ ሰፊ ምርምር እና ሳይንሳዊ ጥናት የሚያስፈልገን አይደለም:: ምክንያቱም ድህነት እራሱ በአይን የሚታይ ነገር ስለሆነ ነው:: በእርግጥ ስለድህነት ስፋት መጠንና ስርጭት፣ ስለድህነት መንስኤዎች፣ ድህነትን ለመቀጋት ስለሚያስችሉ እርምጃዎች በሳይንስ የተደገፈ ምርምር እና ጥናት መካሄድ አለበት:: ይህም የሚሆነው መንግስት ለልማት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ ስልቶችና ፕሮግራሞች በጥናት የተደገፉ መሆን ስላለባቸውና በተግባር ያስከተሉትንም ውጤት በየጊዜው ጥናቶች በማድረግ መከታተል ስለሚያስፈልግ ነው::

- በዚህም መሰረት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር አጥኚዎች በተለያየ ጊዜ የተካሄዱ ጥናቶች ድህነት በሃገራችን ምን ያህል አስከፊ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ በግልፅ አሳይተዋል::

- የአንድ ሀገር እድገት መለኪያ ሆኖ በስፋት ሲሰራበት የቆየውን የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ለምሳሌ ብንመለከት ይሄ የሀገራችን 167 የአሜሪካ ዶላር እንደሆነ ይነገራል:: ቅድም በአለም ባንክ ድርጅት እንደተሰላና እጅግ ዝቅተኛ ለኑሮ አስፈላጊ የሆነው መጠን ብንመለከት ይሄ 275 የአሜሪካን ዶላር ሲሆን የኛ ከዚህ ጋር ሲነፃፀር እጅግ አነስተኛ ሆኖ ይገኛል ማለት ነው::

- በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ (Low Income Countries) የሚባሉ ሀገሮች የዜጎቻቸው የነፍስ ወከፍ ገቢ በአማካኝ 330 የአሜሪካ ዶላር እንደሆነ ይነገራል::
- የጤና አገልግሎትን በተመለከተ ከግማሽ በላይ ወይም 55 በመቶ የሚሆነው ህዝባችን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአቅራቢያው የጤና አገልግሎት የማያገኝ ነበር:: በዚህም ምክንያት በህይወት ከሚወለዱ 1000 ህፃናት 117 ወዲያው የሚሞቱ ሲሆን ከቀሪዎቹ

ደግሞ እድሜያቸው 5 ዓመት ሳይሞላ 1/5ኛው እንደሚሞቱ ይታወቃል:: በጤና መጓደል ምክንያት አማካኝ የእድሜ ዘመን በኢትዮጵያ 52 ዓመት እንደሆነ ሲነገር ይሄ በሌሎች ታዳጊ አገሮች 60 በበለፀጉ አገሮች ደግሞ 80 እንደሚደርስ ይታወቃል::

ትምህርትን በተመለከተ እድሜያቸው ለ1ኛ ክረጃ ከደረሱ ልጆች መካከል በኢትዮጵያ የትምህርት ዕድሉን የሚያገኙት 1/3ኛው ብቻ ሲሆኑ ይሄ በአፍሪካ አገሮች ካሉ በአጠቃላይ ሲታይ 70 በመቶ የሚሆኑት የትምህርት ዕድሉን የሚያገኙ በመሆኑ በሃገራችን የትምህርት ዕድል ምን ያህል ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል::

ይድህነት ሁኔታ በገጠሩ ከከተማ ይበልጥ የከፋ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ለዚህም ማስረጃ ለምሳሌ ሆስፒታሎች ጤና ጣቢያዎች ክሊኒኮች እና ትምህርት ቤቶች በአብዛኛው በከተማ አካባቢ ተሰባስበው መገኘታቸው ነው:: ንጹህ የመጠጥ ውሃን የወሰድን እንደሆነ በገጠሩ 1/5 ከሚሆነው ህዝብ በታች ንጹህ ውሃ የሚያገኝ ሲሆን በከተማ 4/5ኛው የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እንደሚያገኝ ይታወቃል:: በምግብ ራሳችንን ያልቻልን በመሆናችንም ምክንያት አብዛኛው ህዝባችን የተመጣጠነ ምግብ እንደማያገኝና ይህም ለህመምና ለሞት ከሚዳርጉ 10 ዋና ዋና መንስኤዎች ውስጥ ተመድቦ የሚገኝ ነው::

በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን በዘንድሮው አመት በቤተሰብ ደረጃ የተካሄደው የመስክ ጥናት ውጤት ገና እየተጠበቀ ቢሆንም በባለስልጣን መስሪያ ቤት ቀደም ብለው የተጠኑ ጥናቶች (የቆዩ ቢሆንም) እንደሚያመለክቱት በገጠሩ ኢትዮጵያ አማካኝ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአመት 460 የኢት. ብር መሆኑ ይህም በወር ሲሰላ ከ40 ብር በታች ነበር::

በከተማ ነዋሪ የሆነውን ህዝብ የድህነት ሁኔታ በተመለከተ በ1982 ዓ.ም. በአለም ዓቀፉ የስራ ድርጅት (ILO) የተካሄደው ጥናት እንዳመለከተው ደግሞ 63 በመቶ የሚሆነው የከተማ ህዝብ አማካኝ የወር ገቢው ከ100 ብር በታች እንደነበረ ታውቋል::

የአለም ባንክ ልዑካን ቡድን በሽግግሩ መግቢያ ወቅት በቀን ከ2100 ካሎሪ የሚሰጥ ምግብ ለመግዛትና ሌሎች ኪራይ፣ ትራንስፖርት፣ ሳሙና የመሳሰሉ መሰረታዊ ፍጆታዎችን ለመሸፈን 5 አባላት ያለው በከተማ የሚኖር ቤተሰብ በወር 244 ብር

እንደሚያስፈልገው በማስላት ባደረጉት ጥናት ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከሚኖረው ህዝብ 60 በመቶ የሚሆነው ይህን ማሟላት የማይችል ድሃ ህዝብ እንደሆነ ዘግበዋል::

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢኮኖሚክስ ዲፓርትመንት እና የመካነ ልማት ጥናት ተቋም ከኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር በተወሰኑ በታዎች እና ለናሙና በተመረጡ ቤተሰቦች ላይ በተከታታይ የተካሄደው ጥናት እንዳመለከተውም ለናሙና ከተመረጡ ቤተሰቦች ውስጥ 61 በመቶ የሚሆኑት በፍፁም ድህነት ውስጥ እንደሚገኙ ታውቋል::

- በዚህም መሰረት የተለያዩ መለኪያዎች ተወስደው ቢታዩም ከኢትዮጵያ ህዝብ ባጠቃላይ 60 በመቶ የሚሆነው በፍፁም ድህነት ውስጥ የሚገኝ እንደሆነ ይገመታል::

## 3.1 ድህነት የሰፈነባቸው ቦታዎች ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች

- ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው እስካሁን የተጠኑ ጥናቶች አንድም ጊዜ ያለፈባቸው ወይም ደግሞ ያልተሟሉ እና ባብዛኛው ግምታዊ በሆኑ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: ሆኖም እነዚህ ጥናቶች ከሞላ ጎደል እንደሚያመለክቱትና በሌሎች በተመሳሳይ እድገት ደረጃ በሚገኙ ሀገሮች የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት:

  - ድህነት ባብዛኛው በገጠሩ ህዝብ ላይ ያመዘነና የከፋ እንደሆነ ይታወቃል::

  - ሌላው በሁለተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ድህነት ባብዛኛው የሚያጠቃው በተለይ ሴቶችንና ህፃናትን መሆኑ ነው::

- ከዚህ ውጪ አስቀድሞ እንደተገለፀው መንግስት ስለሀገራችን ህዝብ ድህነት ሁኔታ በሰፋተና በጥልቀት በየጊዜው ጥናት ለማካሄድና በኑሮ ሁኔታ ላይ ክትትል ለማድረግ አስፈላጊ ዝግጅቶች የተጠናቀቁ ሲሆን ለዚህም ሲባል በቅርቡ የኑሮ ሁኔታ ክትትል ስርዓት ተመስርቶ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል:: ሆኖም ይህ አዲስ ጅምር እንቅስቃሴ በመሆኑ ስለሀገራችን ድህነት ሁኔታ፣ ድህነት ስለሰፈነባቸው በታዎች ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች በዝርዝር መናገር የሚቻለው በያዝነው አመት በማ.ስ.ባ. የተካሄደው ጥናት ወጥቶ በዚህ ላይ ተጨማሪ ዝርዝር ናቶች ሲካሄዱ እና ወደፊትም በየአመቱ እንደሚካሄዱ በታቀዱ የኑሮ ሁኔታ የመስክ ጥናቶች ውጤት ላይ በመመስረት ይሆናል::

# 4. የድኅነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ ዓላማ ይዘት እና አዘገጃጀት

## 4.1 የድቅስ ሰነድ አላማ

የድኅነት ቅነሳ ስትራቴጂ (ድቅስ) ሰነድ በመስከረም ወር1991 ዓ.ም. በዓለም ባንክና በአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የታወጀ አዲስ መርህ ግብር ነው:: የድቅስ ሰነድ መርሃ ግብር በታዳጊ ሀገሮችና በአለም ዓቀፍ የፋይናንስ ተቋሞቹ መካከል ከዛም በማለፍ ከበለጸጉ ሀገሮች ጋር ወደፊት የሚደረጉትብብሮች በዋናነት ድህነትን በመቀነስ ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርግ እንደሆነ ይጠበቃል::

የሰነዱ ፅንሰ-ሀሣብ የተጠነሰሰው በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማቱ ሲሆን በድኅነት ላይ በአዲስ መንፈስ ለመዝመት ለተነሱበት ዓላማ ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው:: በዚህም መሠረት ተቋማቱ ከዚህ ቀደም ከታዳጊ ሀገሮች ጋር ለሚያደርጉት የትብብር ስምምነት እንደ መሠረት ሆኖ ያገለግል የነበረውን የፖሊሲ ሰነድ በድቅስ ሰነድ እንዲተካ አድርገዋል::

የድንቅ ሰነድ አጠቃላይ ዋና ዋና አላማዎች የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. የአለም ባንክና የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ለታዳጊ ሀገሮች በአነስተኛ ወለድ የሚሰጡት ብድር ድህነትን ለመቀነስ ለሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ እንዲውል ለማድረግ፣

ለ. በድሃ ሀገሮች ላይ ያለው ከፍተኛ የእዳ ጫና በአፋጣኝ እንዲቀንስ ለማድረግ፣

ሐ. የታዳጊ ሀገሮች መንግሥታት በእዳ ቅነሣ የሚያገኙትን ገንዘብና ወደፊት በድጐማ የሚያገኙትን ብድርም ሆነ እርዳታ በተገቢ መንገድ ያለባቸውን የድህነት ችግሮች ለማቃለል እንዲያውሉ ለማድረግ፣

መ. ውጤታማ የሆነ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ እንዲቀየስ ለማድረግ ናቸው::

በአጠቃላይ የድቅስ ሰነድ በከፍተኛ የእዳ ጫና የሚሰቃዮ ድሃ ሀገሮች ከፊል የእዳ ስረዛ እና ደጓሚ ቀጣይ ብድርና እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው:: ሰነዱ ይህን አመቺ ሁኔታ የሚፈጥረው ሀገሮቹ ያለባቸው ጫና ተቃሉላቸው ድህነትን በተጠናከረ መንገድ መዋጋት እንዲችሉ ለማድረግ ታስቦ ነው:: በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ የእዳ ቅነሣ ተጠቃሚ ሀገር

### የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

በድቅስ ሰነድ ድህነትን ለመዋጋት የሚያስችለውን ስትራቴጂ በመቀየስ ከእዳ ስረዛ የሚገኘው ቁጠባ በምን ምን ፕሮግራሞች ላይ ውሎ ድህነትን ለመቀነስ እንደሚረዳ ማሳየት አለበት።

የድቅስ ሰነድ በማዘጋጀት የእዳ ስረዛ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ድሀ ሀገሮች በጠቅላላው41 ሲሆኑ ሰነዱን በተገቢው ሁናቴ አዘጋጅተው ተግባራዊ በሚያደርጉበት ሂደት በጠቅላላው 97 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚደርስ የእዳ ስረዛ እንደሚደረግላቸው ይጠበቃል። የታቀደው የእዳ ስረዛ ሀገሮቹ ያለባቸውን እዳ ሙሉ በሙሉ የሚያጠፋ ባይሆንም ያለባቸው ጫና ተቃሎ ድህነትን ወደሚቀንስ የልማት ጉዳና ያሸጋግራቸዋል ተብሎ ይታመናል።

## 4.2 የድቅስ ሰነድ ይዘት

የድቅስ ሰነድ አዲስ የልማት መርሃ ግብር (approach) እንጂ አዲስ የልማት ንድፈ ሃሣብ (theory) አይደለም። ሰነዱ ምንም እንኳ እስካሁን በታዳጊ ሀገሮች በተለያዩ ወቅት የተሞከሩና እምብዛም ውጤት ያላስገኙ የተለያዩ የልማት ቲዎሪዎችን የሚተካ አዲስ ንድፈ-ሃሣብ የያዘ ባይሆንም የተለያዩ መሠረታዊ መርሆዎችን ያቀናጀ በባህረው ካለፉት የልማት ስትራቴጂዎች አዘገጃጀት ሂደት የሚለይ በመሆኑ እንደ አዲስ መርሃ- ግብር ወይም የልማት አካሄድ ዘዴ ይቆጠራል።

የድቅስ ሰነድ ከዚህ ቀደም ከነበሩ መርሃ-ግብሮችና የስትራቴጂ አዘገጃጀት ሂደት ከሚለይባቸው ዋና ዋና ባህርያትና በነዚህም ምክንያት ሰነዱን ልዩ ወይም አዲስ የሚያሰኙት ይዘቶች እንደሚከተለው በተራ ተተንትነው ቀርበዋል።

### ሙሉ በሙሉ ድህነት ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ

የድቅስ ሰነድ በመጀመሪያ ደረጃ የሚታወቀው ሙሉ በሙሉ ድህነትን በመቀነስ ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ መሆኑ ነው። ሰነዱ የድህነት ጉዳይ ታዳጊ ሀገሮች አጠቃላይ የፖሊሲ ማእቀፍ ውስጥ ቁልፍ ቦታ እንዲኖረው የሚያረጋግጥ ነው። በዚህም ምክንያት በታዳጊ ሀገሮችና በቀረው አለም አቀፍ ሕብረተሰብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት አዲስ መሠረት እንዲይዝ የሚያደርግ ይሆናል።

ድህነትን ለመቀነስ የሚደረግ ጥረት አዲስ ባይሆንም የድቅስ ሰነድ በተጠናከረና በዋናነት የልማት አጠቃላይ ዋና ትኩረት በድህነት ላይ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ይህም ማለት ሌሎች የልማት ዓላማዎች (ለምሳሌ የኢኮኖሚ መረጋጋት፣ የበጀት ጉድለት መወገድ፣ ምርታማነት፣ ወዘተ) ለድህነት ቅነሣ ዓላማ ተገዥ ይሆናሉ ማለት ነው። በዚህም ምክንያት

የሀብት ወይም የመንግሥት በጀት አመዳደብ ቅድሚያ መመዘኛ በጀቱ የሚመደብለት ለድህነት ቅነሣ ከሚያደረገው አስተዋጽኦ አንፃር በዋናነት የሚታይ ይሆናል::

ሰነዱን በማዘጋጀት ሀገሮች የሚያገኙትን የእዳ ቅነሣ ሙሉ በሙሉ በድህነት ቅነሣ ፕሮግራሞች ላይ እንዲያወሉ ይጠበቃል:: በዚህም ምክንያት የድቅስ ሰነድ ድህነትን ለመዋጋት ተጨማሪ ገንዘብ በሥራ እንዲውል የሚያደርግ ይሆናል:: ሀገሮች ያለባቸው የእዳ ጫና በመቀነሱም መንግሥቶቻቸው ካላቸው በጀት ድህነትን ለመቀነስ ለሚረዱ ማህራዊ አገልግሎቶች ሊመድቡ የሚችሉትን ድርሻ ከፍ ማድረግ ያስችላቸዋል::

በተጨማሪም ድሀ የተባሉት ሀገሮች ወደፊት ከዓለም ባንክ እና ከአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት በቀጣይነት የሚያገኙት ደጓሚ ብድር (Concessional loan) ይህንኑ ሰነድ ተግባራዊ ለማድረግ በሚረዳ መልኩ የሚሰጥ በመሆኑ በድህነት ላይ የሚደረገው ርብርቦሽ እንዲጠናከር የሚያደርግ ይሆናል:: አንዳንድ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ካሁኑ ወደፊት ከሀገሮች ጋር የሚያደርጉትን ትብብር በዚህ ሰነድ ላይ እንደሚመሠርቱ ቃል በመግባታቸው ሰነዱ ከመንግሥት በጀት እና ከአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ከሚገኝ ገንዘብና ትኩረት በተጨማሪ አጠቃላይ የውጭ እርዳታ በዋናነት በድህነት ቅነሣ ላይ እንዲውል የማድረግ እድሉ ከፍተኛ ነው::

## በሀገሮች ባለቤትነት እና መሪነት የሚዘጋጅ መሆኑ

የድቅስ ሰነድ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በንቃት በሚያደርጉት ተሳትፎ በመንግሥት መሪነት የሚዘጋጅ በመሆኑ እያንዳንዱ ሀገር ለሚያዘጋጀው ሰነድ ብሔራዊ ባለቤት እንደሚሆን ይጠበቃል:: ይህም የድቅስ ሰነድ ከዚህ ቀደም ከነበሩ የልማት መርሃ ግብሮች የሚለይበት አንዱ ዋናው ባህርዩ ነው::

ከዚህ ቀደም በነበረው አሠራር የዓለም ባንክ እና የዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ታዳጊ ሀገሮች የሚመሩባቸውን ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች እራሳቸው እያዘጋጁ ተግባራዊ እንዲሆኑ በሀገሮች ላይ ጫና ያደርጉ ስለነበር የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ባለቤት እነዚሁ የዓለም አቀፉ የፋይናንስ ተቋማት ነበሩ:: ከዚህ በተፃራሪ የድቅስ ሰነድ ሙሉ በሙሉ ድሃ በተባሉት ታዳጊ ሀገሮች ባለቤትነት እንደሚዘጋጅ ይጠበቃል:: በዚህም ምክንያት ከዚህ ቀደም በዓለም አቀፍ ተቋማቱ በየሀገሮች ያሉ ልዩነቶችን ሳያገናዝቡ የተዘጋጁ አንድ ወጥ የሆኑ የፖሊሲና ፕሮግራም መርሃ

## የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

ግብሮች ያስከተሉትን ችግሮች የድቅስ ሰነዶች በየሀገሮቹ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርተው የሚያዘጋጁ በመሆናቸው ችግሮቹን ከወዲሁ እንደሚያስቀሩ ይጠበቃል።

ዶ/ር ብርሃኑ (1993) እንዳሉት የድቅስ ሰነድ ባለቤት ታዳጊ ሀገሮች እራሳቸው መሆኑ በሰነዱ የተካተቱ ፕሮግራሞች አፈፃጸም ስኬታማነትን የሚያጠናክር ይሆናል። በሌላ በኩል ሰነዱ በየሀገሮቹ መሪነት መዘጋጀቱ ዋና ዋና የድህነት ችግሮች ተገቢ በሆኑ እርምጃዎች እንዲቀረፉ የሚዘጋጀው ስትራቴጂ ሀገር በቀል በመሆኑ ተስማሚና ውጤታማ የሚሆንበት እድል ከፍተኛ ነው።

በመርህ ደረጃ ከላይ እንደተብራራው የድቅስ ሰነድ አዘጋጅና ባለቤት ታዳጊ ሀገሮቹ ራሳቸው እንደሆኑ ቢወሰንም በተግባር ግን መርሁ ብዙ መሰናክሎች እንደሚያጋጥሙት ይጠበቃል። በመጀመሪያ ደረጃ የሰነዱ አዘጋጅና ባለቤት እያንዳንዱ ታዳጊ ሀገር ይሁን ሲባል በየሀገሮቹ ያሉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሰነዱ ዝግጅት በንቃት ተሳትፈው አዘጋጅና ባለቤት ይሁኑ ማለት ነው። ሆኖም በአብዛኞዎቹ ታዳጊ ሀገሮች ያለው የዲሞክራሲ መጉልበት ገና በእንጭጩ ላይ የሚገኝ በመሆኑ መንግሥት በሰነዱ ዝግጅት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፍበት ደረጃ ውስን ሊሆን ይችላል።

ሌላው የሀገሮችን የሰነዱ ባለቤትነት ሊቀንስ ወይ አጠያያቂ ሊያደርገው የሚችለው ጉዳይ ሰነዱ ዞሮ ዞሮ በአለም ባንክ እና በአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ተቀባይነት ማግኘት ያለበት መሆኑ ነው። የአለም አቀፉ ተቋማት ሰነዱ በአጥጋቢ ሁኔታ የተዘጋጀ አይደለም ብለው ከወሰኑ ኢትዮጵያ የእዳ ስረዛ እና ቀጣይ ደጎሚ ብድር የምታገኝበት ሁኔታ ሊስተጓጉል ይችላል። በዚህም ምክንያት ሰነዱ ተግባራዊ ሳይሆን ሊቀር ይችላል። በተለይም የአለም አቀፉ ተቋማት ከዚህ በፊት ያራምዷቸውን ፖሊሲዎች በተዘዋዋሪ መንገድ በሀገሮች በሚዘጋጁ ሰነዶች ውስጥ እንዲካተቱ ግፊት ወይም ሙከራ የሚያደርጉ ከሆነ የሰነዶቹ ባለቤት ሀገሮቹ ራሳቸው መሆኑ አጠ ያያቂ ይሆናል።

የድቅስ ሰነድ በተግባር ሲውል አንዳንድ መሰናክሎች እንደሚያጋጥሙት ቢታወቅም፣ መርሁ ከዚህ በፊት ከነበሩ አሠራሮች በተለየ ሀገሮች በመሪነት የራሳቸው የሆነ ስትራቴጂ እንዲያዘጋጁ ቢያንስ በመርህ ደረጃ ያስቀመጠ በመሆኑ ታዳጊ ሀገሮቹ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ይህ መርህ የተቻለውን ያህል በያዛቸው መርሆች መሠረት ተግባራዊ እንዲሆን የበኩላቸውን የሀላፊነት ድርሻ መወጣት ይኖርባቸዋል።

በሕዝባዊ ተሳትፎ የሚዘጋጅ መሆኑ፣

ከላይ ከተገለፀው የሀገሮች ባለቤትነት መርህ ጋር በቅርብ የሚዛመድ የድቅስ ሰነድ ሌላው ባህሪ ሰነዱ የሚዘጋጀው በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ንቁ ተሳትፎ መሆኑ ነው:: በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂው ዝግጅት ላይ መንግሥት ማሳተፍ ያለበት ድሃው ህብረተሰብና እሱን የሚወክሉ ተቋማት፣ የቀበሌና የወረዳ መስተዳድሮች፣ ፖለቲከኞችና ተቃሚዎችን ጨምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ መንፈሳዊ መሪዎችን፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ የሰራተኛ ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ልዩ ልዩ የሙያ ማህበራትን፣ ተመራማሪዎችን፣ የብዙሃን መገናኛ ተወካዮችን፣ እርዳታ ሰጪ ድርጅቶችንና ሌሎች ቀሪ የህብረተሰብ ክፍሎችን ይጨምራል::

በድቅስ ሰነድ መርህ መሠረት ሕዝባዊ ተሳትፎ ማለት ከላይ የተዘረዘሩት የህብረተሰብ ክፍሎች የሰነዱ አዘገጃጀት ሂደት እና የሰነዱ ይዘት ላይ ወሳኝ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ማለት ነው:: መንግሥት እነዚህን ህብረተሰብ የሚያሳትፍበት ደረጃ የምክር ወይም ሃሣብ የመጠየቅ ሂደት ሳይሆን አብሮ በጋራ የማቀድ፣ የመወያየት፣ የማጥናት እና የፖሊሲ ሃሣቦች የማፍለቅ እና ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገዶች የመቀየስ ሂደት መሆን ይኖርበታል:: በዚህ መልክ የሚዘጋጀው ስትራቴጂ ባለቤት ሕዝቡ ራሱ ይሆንና የባለቤትነት ስሜት ስለሚፈጥርና ሕዝቡ በሚሰጠው ሙሉ ድጋፍ ተግባራዊ ስለሚሆን ስኬታማነቱ የተረጋገጠ ይሆናል ለማለት ያስደፍራል::

ሕዝባዊ ተሳትፎ በድቅስ ሰነድ በመርህ ደረጃ የተያዘ ሲሆን ተግባራዊነቱ ግን ሀገሮች እንደደረሱበት የዲሞክራሲ ስርዓት መጐልበት ደረጃ የሚለያይ ይሆናል:: የዲሞክራሲ ስርዓት በተሻለ ደረጃ ሰፍኖ የሚገኝባቸው ሀገሮች የሚገኙ መንግሥታት ሕዝባቸውን በንቃትና ግልጽ በሆነ መድረክ ሁሉንም ወገኖች አካተው ሰነዱን እንደሚያዘጋጁ ሲጠበቅ ዲሞክራቲክ ያልሆኑ መንግሥታት የአለም አቀፉ ተቋማት ግዴታን ለማሟላት ብቻ ውስን የሆኑና የሁሉንም ሕብረተሰብ ክፍሎች የማያሳትፉ ጠባብ መድረኮች በመፍጠር ጉዳዩን አድበስብሰው ለማለፍ የሚያስችላቸውን መንገድ እንደሚፈጥሩ ይገመታል:: የሰነዱ ዝግጅት በተገቢ ሕዝባዊ ተሳትፎ በማይመሠረትበት ወቅት ለሚዘጋጀው የድህነት ትነሣ ስትራቴጂ ሕዝቡ የባለቤትነት ስሜት ስለማይኖረው ስትራቴጂው በአለም አቀፉ ተቋማት ተቀባይነት ቢያገኝ እንኳ ስኬታማነቱ አጠራጣሪ ይሆናል::

## የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በድቅስ ሰነድ ዝግጅት በንቃት መሳተፋቸው ከሚያስገኘው ጥቅሞች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ

1ኛ. ድሃው የህብረተሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው የሚለውን በሚገባና በተሟላ ሁኔታ ለመለየት፣

2ኛ. አንገብጋቢ የድህነት ችግሮች ምንድንናቸው የሚለውንና ቅድሚያ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን ችግሮች ለመለየት

3ኛ. ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለመለየት፣ በተጨማሪም

4ኛ. ሕዝቡ የኔ የሚለው ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ለተግባራዊነቱ የሁሉንም ህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማግኘቱ ናቸው::

ሕዝባዊ ተሳትፎ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ቢታወቅም ከዲሞክራሲ ስርዓት አለመጎልበት በተጨማሪ በመንግሥትም ሆነ በህብረተሰቡ በኩል ያለው የአቅም ውስን መሆን ሌላው የሕዝባዊ ተሳትፎ ደረጃን የሚገድብ ችግር ነው:: ሆኖም ሕዝቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው አስፈላጊ ቅስቀሳ በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲካሄድ ቢበረታታ ሕዝቡ በፈቃደኝነትና በፍላጐት ለመሳተፍ ስለሚነሣሣ መንግሥት በገንዘብና በሰው ሀይል እጥረት የተነሣ የሚያደርገው ሕዝባዊ ተሳትፎ የተገደበ እንዳይሆን ይረዳል:: የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችም እርስ በርስ የሚያደርጉት መደጋገፍና ትብብር ለመርሁ ስኬታማነት አስተዋጽዖ ይኖረዋል::

## ሁሉን አቀፍ ሰፋትና ይዘት ያለው መሆኑ

በድቅስ ሰነድ ድህነትን ለመዋጋት የሚዘጋጀው ስትራቴጂ የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ሁኔታን፣መዋቅራዊ ችግሮችን፣ የየሴክተሮች ሁኔታን ማህበራዊ ጉዳዮችን በአንድ ላይ በመዳሰስ የድህነት ብዙ ወገን ባህሪዎችን ባገናዘበ መልኩ የሚዘጋጅ ነው:: ይህም ከሚያካትታቸው ውስጥ ለምሳሌ፣

በአጠቃላይ ፖሊሲ ማዕቀፍ

- የዋጋ ንረት መጠን
- የጠቅላላ ምርት ዕድገት
- የውጭ ምንዛሪ ግኝትና ፍላጐት መጣጣም
- የሕዝብ እድገትና ስብጥር

በፋይናንስ ፖሊሲና በጀት

- የመንግሥስት ገቢ መጠን
- ከውጭ በእርዳታ፣ በብድር፣ ወዘተ የሚገኝ ሃፋይናንስ ሁኔታ
- ለልማት ፕሮግራሞችና ድህነት ቅነሣ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልግ ገንዘብ መጠን
- የበጀት ክፍፍል በሴክተር፣ በክልል፣ በኢንቨስትመንትና በመደበኛ ወጪዎች

በመዋቅራዊና ሴክተር ነክ ፖሊሲዎች

- የትኩረት ቅደም ተከተሎችን መወሰን
- የፖሊሲዎች ቅደም ተከተል አፈጻጸም
- ለድሃው ህብረተሰብ የሚሰፉፋ እድሎች

በማህበራዊ ፍትህና እኩልነት

- የሕግ የበላይነት
- በአካባቢ ውሣኔዎች የህብረተሰቡ ተሳታፊነት
- የማህበረዊ ደህንነትና የሥራ ፖሊሲዎች
- ለኋላ ቀር ክልሎች የሚሰጥ ትኩረት

በጥሩ አስተዳደርና የመንግሥት አሠራር

- የመንግሥት በጀት አሠራር፣ ህዝባዊ ተጠሪነት
- ግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር
- የአካባቢ አገልግሎቶች አሰጣጥ
- የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ

የድቅስ ሰነድ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና የመንግሥስት አሠራሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጅ በመሆኑ ሰፋትና ጥልቀት ያለው ሰነድ ይሆናል። በአፈፃፀሙም ወቅት የስኬታማነቱን ሂደት ለመከታተል የሚረዱ ተገቢ አመልካቾችን ሰነዱ የሚያካትት ይሆናል።

የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

## በጋራ ትብብር (ሽርክና) ላይ የተመሠረተ መሆኑ

የድቅስ ሰነድ ዝግጅትና አፈፃፀም የአንድ ወገን ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን መንግሥት፣ ነዋሪ ህብረተሰቡና የውጭ በጐ አድራጊ እና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች በጋራ የሚተባበሩበት ጉዳይ መሆኑ የሰነዱ አንደኛው ልዩ ባህሪ ነው:: ሰነዱ ሲዘጋጅ እነዚህ የተለያዩ ክፍሎች በጋራ መድረክ ተገናኝተው በግልጽነት በሚያደርጉት ውይይትና መግባባት በመንግሥት መሪነት የሚካሄድ እንቅስቃሴ ነው የሚሆነው:: በተመሳሳይ መልኩ በሰነዱ የታቀፈው ስትራቴጂ በተግባር ሲውል ሁሉም የበኩሉን ድርሻ የሚያበረክትበት እንዲሁም በተገቢው መንገድ ስራ ላይ ስለመዋሉ ክትትል የሚያደርግበት ይሆናል:: የሰነዱ የዚህ መርህ ወይም ባህሪ ዓላማ የሚመለከተው ሀገር አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ እና ሀገሪቱ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የምታገኘው አጠቃላይ ሀብት አጠቃቀም ዋና ትኩረት በድህነት ቅነሣ ላይ እንዲሆን ለማድረግ ነው::
በዚህ ባህርዩ የተነሣ የድቅስ ሰነድ፣

- የሀብት ማፈላለጊያ መንገድ ወይም መሳሪያ
- የእርዳታ ቅንጅት መፍጠሪይ
- የመንግሥት ወጪ አስተዳደር ማሻሻያ
- ለዲሞክራሲያዊ አሠራር መጐልበት የሚያገለግል ይሆናል::

በተጠቀሰው መልክ የሚዘጋጅ ሰነድ ወይም ስትራቴጂ ተግባራዊ ሲሆን የተጠቀሱት የተለያዩ ክፍሎች የሚያደርጉት የልማት እንቅስቃሴ በሰነዱ የሚመራ ይሆናል:: በዚህም ምክንያት የመንግሥት በጀት ምደባና ድልድል፤ በእርዳታ የሚገኝ ሀብት የሚውልበት መንገድ፣ የመንግሥት የተለያዩ መዋቅሮች የሚየደርጉት እንቅስቃሴ፣ የሀገር ውስጥ በጐ አድራጊ ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ወዘተ በሙሉ በሰነዱ የሚመሩ ይሆናሉ ማለት ነው::

## ውጤት ግኝት ላይ አትኩሮ የሚዘጋጅ መሆኑ

ከዚህ ቀደም በነበረው አሠራር የልማት ስትራቴጂ ሲዘጋጅ እና አፈጻጸሙ ላይ ክትትል ሲደረግ የነበረው ትኩረት የግብዓቶች አፈጻጸምና የተከናወኑ ስራዎች ሂደት ላይ ነበር:: በድቅስ ሰነድ የሚካተተው ስትራቴጂ ይዘት ከፕሮግራሞች በሥራ መዋል ባሻገር የሚያስገኙት ውጤት ላይ የተመሠረተ ሲሆን የስትራቴጂው አፈጻጸም ስኬታማነት የሚለካው የውጤት አመልካች በሆኑ መለኪያዎች ነው::

ለምሳሌ፣

ከዚህ በፊት ትምህርትን ለማስፋፋት በሚወጣ ስትራቴጂ የሚደረገው ትኩረት ምን ያህል ት/ቤቶች እንደሚሠሩ፣ ምን ያህል አስተማሪዎች እንዲመደቡና፣ የሚመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር መጠን ላይ ነበር። የስትራቴጂውም አፈፃፀም የሚለካው በነዚህ መለኪያዎች ነበር። በድቅስ ሰነድ መርህ መሠረት የስትራቴጂው ትምህርት አካል ዋና ትኩረት የሚሆነው ምን ያህል ሰዎች/ልጆች ትምህርት በማግኘት ማንበብና መጻፍ ቻሉ፣ ወይም በአንድ መስክ እውቀት አገኙ የሚለው ላይ ነው። በመሆኑም የስትራቴጂው ስኬታማነት የሚለካው በሥራ ላይ በዋለው ግብአቶች ወይም የተሠሩ ስራዎች ሳይሆን እነዚህ በተግባር በመዋላቸው የተገኘው ውጤትን በመዳሰስ ይሆናል።

ሰነዱ ሲዘጋጅ ዋና ዋና የውጤት አመልካቾችን የሚይዝ ሲሆን እነዚህ መለኪያዎች በተለይ የስትራቴጂው አካሉች የሚቀየሱ ፕሮግራሞችን ለመንደፍና አፈጻጸም ለመከታተል የሚጠቅሙ ናቸው። ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሉች በሰነዱ ዝግጅት ከሚያደርጉት ተሳትፎ አንደኛው እነዚህን አመልካቾች ለይቶ ማውጣትና ሰነዱም በተግባር ሲውል አፈጻጸሙን በተያዙት መለኪያዎች መሠረት መከታተል ነው። የድቅስ ሰነድ በውጤት ላይ ማተኮሩ በተለምዶ ከነበሩት አሠራር የሚለይበት ባህሪውና ለውጤ ታማነቱ የተሻለ አስተማማኝነት እንዲኖረው የሚያደርግ መሠረት ነው።

## 5. የድቅስ ሰነድ ለኢትዮጵያ የሚኖረው ጠቀሜታ

1. ለኢትዮጵያ ባለባት የእዳ ጫና ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ በእዳ የተደቆሱ ድሃ ሀገሮች ከሚባሉት ጎራ ተመድባ ትገኛለች። የድቅስ ሰነድ ለኢትዮጵያ የሚኖረው ጠቀሜታ ሲነሣ በመጀመሪያ ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ይኸው ኢትዮጵያ ያለባት እዳ ጫና ከፍተኛ መሆኑና የእዳ ቅነሣ ወይም ስረዛ ካላገኘች ኢትዮጵያ የምታደርጋቸው የልማት ጥረቶች ውጤታማ ሳይሆኑ ተጨናግፈው የሚቀሩበት እድል ከፍተኛ መሆኑ ነው። በኢኮኖሚ የበለፀጉ ሀገሮች እንደኢትዮጵያ ላሉ ድሃ ሀገሮች የሚሰጡት የእዳ ቅነሣ የድቅስ ሰነድ ዝግጅትን እንደ ቅድመ-ሁኔታ ያስቀመጡ ስለሆነ ኢትዮጵያ የእዳ ቅነሣ እንድታገኝ መንግሥት የግድ ሰነዱን መዘጋጀት አለበት ማለት ነው።

## የእዳ ጫና የሚየስከትለውን ችግር በምሳሌ ለማስረዳት

- ለኢትዮጵያ ጠቅላላ የእዳ መጠን ከ5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ነው::
- ኢትዮጵያ ሸቀጦችን ወደ ውጭ በመላክ ከውጭ ንግድ የምታገኘው ገቢ በዓመት በአማካይ ወደ 1.6 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ይደርሳል::
- ኢትዮጵያ ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባቸው ሸቀጦችና ጥሬ እቃዎች መጠን ወደ ውጭ ከምትልከው በሶስት እጥፍ ይበልጣል::
- ይህም ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዳለባት በግልጽ ያሳያል::
- ሆኖም ኢትዮጵያ የእዳ አገልግሎት ክፍያ (ከዋናው ተመላሽና ወለድ ለመሸፈን) በዓመት እስከ 250.0 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል:: ስለዚህም በመጀመሪያ ደረጃ ከውጭ ንግድ ከምታገኘው ገቢ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገር የምታስገባቸውን እቃዎች ወጪ መሸፈን አትችልም፡፡ ከዚህ ባሻገር ከምታገኘውን መጠነኛ የውጭ ምንዛሪ ከ15 በመቶ በላይ የሆነውን እዳ ለመክፈል ስለምታውለው ችግሩ የተባባሰ ይሆናል::

2. ሌላው የድቅስ ሰነድ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የሚሆንበት ምክያት የሰነዱ ዋነኛ ትኩረት ድህነትን በመቀነስ ላይ መሆኑ ነው:: ድህነት በኢትዮጵያ ተንሠራፍቶ የሚገኝና ጥልቅ መሠረት የያዘ በመሆኑ ድህነትን የሚዋጋ ስትራቴጂ ለኢትዮጵያ ወሳኝ ጠቀሜታ እንዳለው አጠያያቂ አይሆንም::

ለምሳሌ፣

- በኢትዮጵያ ከሚገኘው ጠቅላላ ሕዝብ ውስጥ 45.5 በመቶ የሚሆነው በፍፁምድህነት ውስጥ የሚገኝና መሠረታዊ የምግብና ምግብ-ነክ ያልሆኑ ፍላጐቶችን ማሟላት የማይችል ነው::
- 64 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ጉልማሳ ሕብረተሰብ መሃይም ወይም ማንበብና መጻፍ የማይችል ነው::
- በሕይወት ተወልደው እድሜያቸው አምስት ዓመት ሳይደርስ የሚሞቱ ሕፃናት ቁጥር ከ6 ሕፃናት 1 ሕፃን ወይም 17 በመቶ የሚሆኑ ናቸው::
- እድሜያቸው ከ1-5 ዓመት ያሉ ሕፃናት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ካልተመጣጠነ ምግብ መንስኤ በሚመጣ የጤና ችግር የሚሰቃዩ ናቸው::
- የንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በአቅራቢያቸው የተዳረሰላቸው ሕዝብ 10 በመቶ ብቻ ሲሆኑ የመፀዳጃ አገልግሎት ያላቸው ኢትዮጵያን ደግሞ 1 በመቶ እንኳ አይሞሉም::

ድህነትን ለመቀነስ የሚደረግ ጥረት አዲስ ባይሆንም የድቅስ ሰነድ በተጠናከረና በዋናነት የልማት አጠቃላይ ዋና ትኩረት በድህነት ላይ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ይህም ማለት ሌሎች የልማት አላማዎች (ለምሳሌ፣ የኢኮኖሚ መረጋጋት፣ የበጀት ጉድለት መወገድ፣ ምርታማነት፣ ወዘተ) ለድህነት ቅነሣ ዓላማ ተገዥ ይሆናሉ ማለት ነው። በዚህም ምክንያት የህብት ወይም የመንግሥት በጀት አመዳደብ ቅድሚያ መመዘኛ በጀቱ የሚመደብለት ጉዳይ ለድህነት ቅነሣ ከሚያደርገው አስተዋጽኦ አንፃር በዋናነት የሚታይ ይሆናል። ስለዱ በኢትዮጵያ የድህነት ጉዳይ አጠቃላይ የፖሊሲ ማእቀፍ ውስጥ ቁልፍ ቦታ እንዲኖረው የሚያረጋግጥ ስለሆነ ጠቃሚነቱ አጠያያቂ አይሆንም።

3. መንግሥት በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደገለፀው ድህነትን መቀነስ የሀገራችን ዋነኛ የልማት ዓላማ መሆኑ ሌላው የድቅስ ሰነድ ለኢትዮጵያ የሚኖረውን ጠቀሜታ የሚያመላክት ጉዳይ ነው። በመንግሥት አመለካከት መሠረት፣

- የግብርና መር ኢንዱስትሪላይዜሽን ስትራቴጂ በገጠሩ የሚገኘው ድርሰ አደር ኑሮ ሁኔታን በማሻሻል ላይ ያተኮረ በመሆኑ መንግሥት አጠቃላይ የልማት አቅጣጫ ሂደታችን ድህነትን በመዋጋት ላይ ያተኮረ ነው ብሎ ስለሚያምን፣
- የመንግሥት አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲና በተለያየ ወቅት የወጡ የመንግስት የሴክተር ፖሊሲዎች (የትምህርት ፖሊሲ፣ የጤና ፖሊሲ፣ ወዘተ) አጠቃላይ በየዘርፉ የሚኖረው የእድገት አቅጣጫ ድህነትን በመቀነስ ላይ መሆኑ በማያወላውል መልክ በማስቀመጣቸው።
- መንግሥት በተግባር ያዋላቸው የልማት ፕሮግራሞች (ሁለተኛው የአምስት ዓመት የልማት መርሃ-ግብር፣ የኢትዮጵያ የማህበራዊ ተሃድሶና ልማት ፈንድ፣ የኤክስቴንሽን ፕሮግራም፣ (በወዘተ) የተቀረጹት ወይም ዓላማቸው አድርገው የተነሱት ድህነትን ለመቀነስ በመሆኑ፣

የድቅስ ሰነድ በስራ መዋል ከዚህ ቀደም የተጀመሩ የተለያዩ የልማት ሙከራዎችን የተዋሃዱና የተደጋገፉ በማድረግ በሀገሪቱ ድህነትን በመዋጋት የሚደረገው እንቅስቃሴ ይበልጥ ተጠናክሮ እንድሄድ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል።

## የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

ከዚህ በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ ጉባዔዎች የሀገሮች መሪዎች ወይም ከፍተኛ ሚኒስትሮች ሕዝቦቻቸውን በመወከል በጋራ ውሣኔዎችን በማስተላለፍ ለሰው ልጅ ብልጽግና ጠቃሚ ናቸው ባሏቸው ጉዳዮች ላይ እርምጃዎችን ለማድረግ የውዴታ ግዴታ ውስጥ ሲገቡ ኢትዮጵያም ከድህነት ጋር የሚያያዙ በርካታ ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በሀገር ደረጃ ስምምነቶችን በፊርማ በማጽደቅ ገዴታ ገብታለች::

ለምሣሌ ለመጥቀስ፣

- እ.ኤ.አ በ1948 ሀገሮች በስምምነት ያፀደቀት "Universal Declaration of Human Rights") ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት መከበር ስምምነት
- እ.ኤ.አ በ2000 የታወጀው የ«ዳካር ትምህርት ለሁሉም» ጉባዔ ውሳኔ ስምምነት
- እ.ኤ.አ በ1995 በኮፐንሄገን የተካሄደው «የዓለም ጉባዔ በማህበራዊእድገት ያስተላለፋቸው ውሣኔዎች» ይህም በአለም ላይ የሚገኘውን የድህነት መጠን በግማሽ ቢያንስ በ2008 (እ.ኤ.አ በ2015) ለመቀነስ የተደረሰውን ስምምነት ያካትታል::

ከላይ የተዘረዘሩትን የዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ኢትዮጵያ በፊርማ ያፀደቀች ስለሆነ መንግሥት የገባበትን ኃላፊነት ለመወጣት የድቅስ ሰነድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይጠበቃል:: ለዚህም ስኬታማነት በተጠቀሱት ስምምነቶች የተቀመጡ ዓላማዎችንና ግቦችን ኢትዮጵያ በየደረጃው ተግባራዊ ለማድረግ በድቅስ ሰነድ መካተት ይኖርባቸዋል:: የነዚህም መካተት ሰነዱ ይበልጥ ተቀባይነት እንዲኖረውና ከፍተኛ የውጭ እርዳታ እንዲገኝ የሚያስችል ይሆናል::

4. ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ከአለም ባንክና ከአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ጋር በመተባበር የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ስታደርግ ቆይታለች:: እነዚህንም ፕሮግራሞች መንግሥት ወደፊት ተግባራዊ እያደረገ እንደሚቀጥል ከዚህ በፊት በወጣው ጊዜያዊ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ሰነድ (I-PRSP) አመልክቷል:: ስለዚህ ከአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ወደፊት ቀጣይ ስምምነት ለማድረግና የድጐማ ብድር ለማግኘት መንግሥት የድቅስ ሰነድ ማዘጋጀቱ ወሳኝ ይሆናል::

   ከዚህ ቀደም የአለም ባንክና የአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ለታዳጊ ሀገሮች ብደር ለመስጠት የሚጠቀሙበት ሰነድ የፖሊሲ መርሃ-ግብር ሰነድ (Policy Framework Paper) ይባል የነበረ ሲሆን ካሁን በኋላ ታዳጊ ሀገሮች ከተቋማቱ ጋር ቀጣይ ስምምነት የሚያደርጉት በድቅስ ሰነድ መሠረት ነው:: ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በመጀመሪያ በእዳ በተዘፈቁ 40 ድሃ

ሀገሮች ሲሆን ከ2ና 3 ዓመታት በኋላ ደግሞ ተጨማሪ 30 ሀገሮች ይህን ሰነድ እንዲያዘጋጁ የሚደረግ ይሆናል (EURODAD 2001)

## የድቅስ ሰነድ ዝግጅትን በቅድሚያ ያጠናቀቁ ሀገሮች

1. ቡርኪናፋሶ
2. ዩጋንዳ
3. ታንዛኒያ
4. ኬንያ

ሲሆኑ በረካታ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች የሰነዱን ዝግጅት በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ ከ15-20 የሚደርሱ ሀገሮች በያዝነው የፈረንጆች ዓመት ማብቂያ ሰነዱን አዘጋጅተው እንደሚያጠናቅቁ ይጠበቃል:: ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማቱ ጋር በመተባበር ከ1938 የሽግግር መንግሥት መመስረት ጀምሮ ባካሄደችው የኢኮኖሚ መዋቅር ማሻሻያ ፕሮግራም የተወሰዱ ፖሊሲዎች በዋጋ እና በገበያ ላይ የነበሩ ማነቆዎችን ማላላት፣ ድጐማዎችን ማንሳት፣ ታሪፍን መቀነስና የውጭ ምንዛሪ በምርት ገበያ ሂደት እንዲተመን ማድረግ ነበሩ:: እነዚህ እርምጃዎች በፊስካል እና የገንዘብ ፖሊሲ ታግዘዋል:: የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲረጋጋ እንዲሁም የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲጐለብት እንዲደረጉ በመግሥቱ ይታመናል:: በተጨማሪም ከፍተኛ የወለድ ምጣኔ አነስተኛ አርሶ አደሮችን መሠረት ያደረገ መጠነ ሰፊ እድገት ለመምጣት አያስችል ብሎ መንግሥት ስለሚይምን በኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ መንግሥት የበጀት ዲሲፕሊን፣ የገንዘብ መጠን እድገት ቁጥጥርን፣ የገንዘብ ግብይትን ደረጃ በደረጃ ወደ ገበይ መር የወጪ እና የገቢ ንግድ ገበይ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል:: በነዚህ መነሻነት በኢትዮጵያ ድህነትን ተቀናጅተው በጋራ ወደፊት በተግባር መዋላቸው እንደሚቀጥል መንግሥት አመልክቷል::

የድቅስ ሰነድ ዝግጅት ኢትዮጵያ ወደፊት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በቀጣይነት ተግባራዊ እንድታደርግ የሚያስችል በመሆኑ መንግሥስ ካለው ፍላጐት አንፃር ሰነዱ በዚህም መስክ አስትዋጽኦ የሚያደርግ ይሆናል::

ሆኖም በድቅስ ሰነድ ዝግጅት በሚደረገው ሕዝባዊ ተሳትፎ ለኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ዎችና ፕሮግራሞች የሚሰጠው አስተያየትና ድጋፍ በሰነዱ በሚገባ መንፀባረቅ ይኖርበታል:: በዚህም መሠረት የሚቀየሰው ስትራተጂ ለነዚህ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የሚሰጠው ትኩረት አሁን መንግሥት ከሚሰጣቸው ትኩረት የሚለይበት ሁኔታ ሊፈጠር ወይም ላይፈጠር ይችላል::

የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

5. ከላይ ከተዘረዘሩተ ጠተሜታዎች በተጨማሪ የድቅስ ሰነድ የሲቪል ማህበረት ከመንግሥት ጋር በጋራ የመሥራት እድል ስለሚፈጥር የመንግሥት አሠራር ግልጽነትን በማዳበርና ሕዝባዊ ተሳትፎን በማጠናከር ለአጠቃላይ ዲሞክራሲ እድገት ትልቅ አስተዋጽዖ እንዲኖረው ይጠበቃል:: የድቅስ ሰነድ ባለቤት መንግሥት እና ሕዝቡ በአንድ ላይ የድቅስ ሰነድ ባለቤት መንግሥት እና ሕዝቡ በአንድ ላይ ስለሚሆኑ በሰነዱ ያተካተቱ ፕሮግራሞች አፈጻጸም በኪታማነተ የተጠናከረ ይሆናለ:: ሆኖም ይህ ጥቅም የሚገኘው ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በሰነዱ ዝግጅት በንቃት ሲሳተፉ እንጂ መንግሥት ብቻውን አዘጋጅና ባለቤት በሚሆንበት ሁኔታ አይደለም:: በሌላ በኩል ህብረተሰቡ በስትራቴጂው ላይ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ ስለሰነዱ ምንነትና አመጣጥ፣ ስለፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘትና አዘገጃጀት፣ ስለአጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ ስለመንግሥት በጀት አሠራር ወዘተ ያለው ግንዛቤ መዳበርና መጠናከር ይኖርበታል::

ኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሞያዎች ማህበር ባቋቋመው የፖሊሲ ምርምር ተቋም አማካይነት በሰነዱ ዝግጅት የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት እቅድ አለው::

በመጀመሪያ ቀቋሙ ያደረገው በሰነዱ ዝግጅት የተሙ አስትዋጽዖ በምን ላይ መሆን የተሻለ ይሆናለ የሚለውን ማጥናት ነው::

የሰነዱ መርህ በሥራ እንደዋለ በWB እና IMF ይፋ ከሆነ በኃላ ጉዳዩ በየሀገሩ በሰፋት በታወቁ በዚህ ሂደት ለመሳተፍ በሀገራችን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍላጐት አሳይተዋል እያንዳንዱ እንቅስቃሲም ጀምረዋል:: ከነዚ ወሰድ ለመቀስ፣

- የPastoralist Frum (በተለምዶ የዛላንክብት አርቢ ህብረተሰብን በመወከል ተቋቁሟል::
- የNGO (መንግሥታዊ ያልሆኑ በጐ አድራጊ ድርጅቶች) PRSP Task Force ወይም የድቅስ ሰነድ ግበረ ሀይል አቋቁመዋል::
- በማህበራዊ ጥናት መድረክ (FSS) በድህነት ጉዳዮች ላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳትፉ ተከታታይ የውይይት መድረኮች በመዘጋጀት ላይ ናቸው
- የንግዱ ማህበረሰብ በአ.አ Chamber of Commerce አማካይነት የዚህን ጉዳይ የሚከታተል ቋሚ ኮሚቴ አቋቁሟል::

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር እንድ ራሱን የቻለ ፕሮጀክት ተቀርጾ ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል:: ይህንንም ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ የ PRSP ወይም የድቅስስ ቢሮ

አቋሙም በሙሉ ጊዜ የሚሰሩ ባለሞያዎችን መድቧል:: ፕሮጀክቱ የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ ዝግጅት አቅም ግንባታና የተሳትፎ ፕሮጀክት ይባላል:: ትኩረቱ Capacity borilsing ናቸው

የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዓላማ ለሀገራችን ተስማሚ የሆነ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያሳተፈ ውጤታማ ሊሆን የሚችል የድህነት ቅነሣ ስትራቴጂ እንዲቀየስ ጥረት ለማድረግ ነው::

ዋና ዋና ተግባራቱም፣

- ህብረተሰቡ ስለ ድቅስ ሰነድ ተገቢ እውቀት እንዲያገኝና በንቃት እንዲሳተፍ የሚያስችል አቅም መፍጠር ለዚህም፣
- ልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳፍ ክልላዊ አውደጥናቶችን ማካሃድ Refone (Awareness worshop)
- ከተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች ለተውጣጡ ስለ ድቅስ ሰነድ፣ ስለፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘትና አዘገጃጀት፣ ስለመንግሥት በጀት አሠራር፣ ወዘተ ስልጠና መስጠት
- የድህነት ችግሮች መንስዔና ቁልፍ የሆነ አብይ ችግሮችና ለመለየት የተለያዩ ስብሰባዎችን/የውደጥናቶችን ማካሄድ (Poverting Dingnostics)
- በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ስለ ድቅስ ግንዘቡን የሚያስተባብሩ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች እንዲተላለፉ ማድረግ
- የድቅስ ሰነድ ዝግጅት የሚመለከቱ ጽሁፎች በተለያዩ ጋዜጦችና በቋሚ የፕሮጀክትና ዜና መጽሔቶች ማውጣት
- የድቅስ ሰነድ ሊይዟቸው ስለሚገባ ፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘቶች የተለያዩ ውይይቶችን ማካሄድ
- የሌሎች ሀገሮች ልምድ የጠቀሱባቸው ፕሮግራሞች ማዘጋጀት
- ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚነሱ ጉዳዮችን በማስተባበር ስለሚመለከተው ሁሉ ማዳረስ ይገኙባቸዋል::

## የሲቪል ማህበረሰቡ ሊያደርጋቸው ከሚችሉ አስተዋጽዖዎች መካከል:-

አጠቃለይ፣

- ኢትዮጵያ ተገቢ የእዳ ስረዛ እንዲታገኝ ከመንግሥት ጐን በመቆም ጥሬ ማቅረብ፣
- ኢትዮጵያ ከውጭ እርዳታ የምታኘውን መጠን እንዲጨምር አመቺ በድቅስ ገቢ ዝግጅት

የድቅስ ሰነድ ፅንሰ ሃሳብ አዘገጃጀት

በድቅስ ሰነድ ዝግጅት

- NGO, የራሳቸውን ፕሮግራሞች መመርመሪያና ድህነት ላይ በይበልጥ እንዲያተኩር በማድረግ ለመንግሥት ፕሮግራሞች (ጥረት) ድጋፍ መስጠት
- ስለድነት ችግሮች ስፋትና መጠን ብሎም መንስኤዎችን ለመንግሥት ማሳወቅ (ያለውን ግንቢ) ማሳደግ፣
- ውጤታማ የሆኑ የድህነት ቅነሣ ፕሮግራሞች (Experiance) ለመንግሥት ልምድ ማካፈል፣
- በመንግሥት ፕሮግራም ያልተዳሰሱ ችግሮችን ማሳወቅ (ያሉ ክፍተቶችንና ችግሮችን)
- ጠቋሚ የድግት አመልካቾችን የመለየት ሥራ ይገኝበታል።

የመንግሥት ሊያደርግ የሚገባው

- ህብረተሰብ የሚወክሉ ድርጅቶችና ተቋሞች ለሰነዱ ዝግጅት በተቋቋሙ መዋቅሮች/ኮሚቴዎች ውስጥ በንቃት የሚሳተፋበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- በመጀመሪያ ደረጃ የድህነት ትንተና (Povery Dignostics) ብሉ በጋራ ከልዩ ልዩ ክፍሎች ጋር ማካሄድ
- የህብረተሰብ ተሳትፎ ከወረዳ እልፎ ቢቻል በየቀበሌው ውይይት እንዳኖር በማድረግ እንነብጋቢ ችግሮች በየደረጃው ወደላይ የሚተላለፋበት መንገድ ቢኖር
- በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሉች ጉልህ ሚና እንዲኖቸው ማድረግ
- ውይይቶችን በመምራት
- ተሳታፊዎችን በመምረጥ
- መንደርደሪያ መወያየቱ ሃሣቦችን በማቅረብ

## የመንግሥት እቅድን በተመለከተ

የውይይት መጀመሪያ የድህነት ችግሮች ቢሆኑ፣ ከወረዳ ይዘት በቀበሌ ቢጀመር 50 ተወካዮች እንቢተኛ ስለመሆን ቁጥሩ ቢጨምር የተለያዩ በመጥራት የጋራ እቅድ እንዲወጣ

የተለያዩ Institutions በመጥራት የጋራ ዕቅድ እንዲወጣ ቢደረግ እንደ ፖለቲካው ሁሉ የኢኮኖሚ አቅጣጫ ተሃድሶ ቢደረግ ያሉ የመንግሥት ፖለቲካዎች ስትራቴጂዎች ላይ ውይይት እየተካሄደ ችግሮች በታወቁና በዚህ መሠረት ቢስተካከሉ::

## 6. የድቅስ ሰነድ አዘገጃጀት ሂደት

### ሀ. የድህነት ሁኔታ ትንታኔ

ውጤታማ የሆነ ፖሊሲና ስትራቴጂ ለመቀየስ ጠለቅ ያለ የድህነት ትንታኔ ማካናወንና የደሃው ህብረተሰብከኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ጋር ያለውን ግንኙነት በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል። ድሃ የሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ማን እንደሆኑ ዋና ዋና መተዳደሪያቸው እና የገቢ ምንጫቸው ምን እንደሆነ፣ ምነ አይነት ሸቀጦችን ለፍጆታ እንደሚያውሉ፣ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ምን ያህል እንደሚያሟሉ፣ ወዘተ በሚገባ መታወቅ አለበት።

ድህነትን ለመዋጋት የሚያቀረቡ ፖሊሲዎች በድህነት ሁኔታ ላይ የሚያስከትሉትን ለውጥ ለማጤን፣ ስለ ድሃው ህብረተሰብ ሰፊ ግንዛቤ የሚያስፈልግ ሲሆን ይህም መተዳደሪያ ገቢያቸው ከየት እንደሚገኝና ገቢያቸውን በምን ላይ እንደሚያውሉ ከሚያስፈልግ ግንዛቤ በተጨማሪ እነዚህ ህብረተሰቦች መንግስት ለሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ለአካባቢያቸው የሚሰጡት ምላሽ ወይም ያላቸው እንድምታ መታወቅ ይኖርበታል። በተጨማሪም ድሃው ህብረተሰብ በእለት ተእለት ኑሮው በስራ የሚገናኛቸው መንግስታዊ ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞች ተለይተው መታወቅና እንዲጠናከሩ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

በድህነት ሁኔታ ላይ የሚደረግ ጥናት ወይም ትንታኔ በአንድ ወቅት ብቻ የካሂዶ የሚቋረጥ ሳይሆን በየጊዜው መካሄድ ያለበትና በጥናቱ የሚገኙ ግኝቶች አዳዲስ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ፣ በተግባር ላይ በመዋል የሚገኙትን ደግሞ ለማሻሻል እና ለማጠናከረ እንዲረዱ ተደርጎ በጥቅም ላይ መዋል ይኖርባቸዋል።

## ድሃ የሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዴት ይለያሉ

ድህነት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ አንፃራዊ ወይም ፍጹም በሆነ መንገድ ሊተረጎም ይችላል። አንፃራዊ ድህነት የሚያተኩረው በገቢ ክፍፍልና በህዝቡ መካከል ናለ የኑሮ ደረጃ ልዩነት ላይ ሆኖ አንድን ግለሰብ፣ ቤተሰብ ወይም ህብረተሰብ፣ ከሌላው ግለሰብ፣ ቤተሰብ ወይም ህብረተሰብ ጋር የሚያነፃፅር ለዚህም አማካኝ ገቢ መጠንን እንደዋና መለኪያ የሚወሰድ ነው።

ፍፁም ድህነት በሌላ በኩል ዋናው ትኩረቱ በመሰረታዊ ፍላጎቶች መሟላት ላይ ሆኖ መለኪያውም በምን ያህል መጠን እነዚህ ፍላጎቶች መጓደላቸውን በመለከት ነው። በዚህ አተረጓጎም መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላሟሉ ግለሰቦች ወይም ቤተሰቦች ድሃ ይባላሉ ማለት ነው። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ ሃገሮች ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጥ የሚገባው ፍጹም ድህነትን በመዋጋት ላይ ወይም በነዚህ ሃገሮች የሚገኙ ህዝቦች መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው በሚሟላበት መንገድ ላይ መሆን አለበት። ለዚህም ዋናው ምክንያቱ አንፃራዊ ድህነት ሁሌም የሚኖርና ባደጉ ሀገሮችም ቢሆን በየአገሮቹ ካለው አማካኝ ገቢ አጅግ አነስተኛ ሆኖ ሊገኝ ስለሚችል በአንፃራዊ ድህነት ጎራ ስለሚመደቡ ነው።

ስለዚህ ድሃ የሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመለየት የመጀመሪያ ደረጃ ድህነት የሚባለው ቃል መተርጎም አለበት ማለት ነው። በአለም ባንክ አተረጓጎም መሰረት ድህነት ማለት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ እራሱ እንዴት እንደሚለካ እንዲሁም ዝቅተኛ የሚባለውስ እንዴት ይወሰናል የሚለው መታወቅ አለበት። ድህነት በኑሮ ደረጃ የሚተረጎም ከሆነ የድህነት መጠን መለኪያ የኑሮ ደረጃ መለኪያ ይሆናል ማለት ነው።

በአሁኑ ወቅት ባለው አሰራር የኑሮ ደረጃ መለኪያ ሆነው በዋናነት የሚያገለግሉት የቤተሰብ የነፍስ ወከፍ ገቢ ወይም ወጪ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ ጤና እድሜና ትምህርት የመሳሰሉ የድህነት አመልካቾችን በሚገባ እንደማያንፀባርቁ ይታወቃል። ለዚህም የነፍስ ወይም ወጪ መለኪያዎች በሌሎች የጤናና የትምህርት አመልካቾች መደገፍ ይኖርባቸዋል። ከድህነት ለመላቀቅ የሚያስችለው የነፍስ ወከፍ ገቢ ወይም ወጪ መጠን የድህነት ስመር ገደብ በመባል ይታወቃል። ከዚህ ገቢ ወይም ወጪ መጠን በታች የሚያገኙ ግለሰቦች ድሃ ይባላሉ ማለት ነው።

## የድህነትን ቅነሳ ስልት ስትራቴጂ ሰነድ

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ውሎ የሚገኘው የድህነት መስመር ለአንድ ጎልማሳ በአመት በአማካይ 165.4 የአሜሪካን ዶላር ወይም 1400 ብረ ገቢ ማግኘት እንዳለበት ሲሆን ከዚህ በታች የሚያገኙ ሁሉ ድሃ ይባላሉ ማለት ነው።

ለአንድ ሀገር ተስማሚ ይሆናል የድህነት መስመር ለመወሰን በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄድ ቤተሰብ ገቢና ፍጆታ የመስክ ጥናት ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል። በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን እ.ኢ.አ በ1999/2000 የተካሄደ የቤተሰብ ገቢና ፍጆታ የመስክ ጥናት ስላለ በዚህ ጥናት ተመስርቶ ከዚህ ቀደም ተካሂዶ በነበረ ተመሳሳይ ጥናት ተመስርቶ ከዚህ ቀደም ተካሂዶ በነበረ ተመሳሳይ ጥናት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀውን በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ የዋለውን የድህነት መስመር ማሻሻል ያስፈልጋል።

መንግስት ድሃ የተባሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት የድህነት መጠን በየክልሉና ከተቻለም ያለውን ስርጭት በሚያጠናበት ወቅት የሲቪል ማኀበራትን ማሳተፍ እንዳለበት በድቅስ ሰነድ መርሀ ተቀምጧል።

በሰነዱ ዝግጅት የሲቪል ማኀበራት ተሳትፎ መጀመር ያለበት የድህነት ትንታኔ ከማድረግ ጀምሮ ይሆናል ማለት ነው። የሲቪል ማህበራት ተሳትፎ ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ውስጥ፣

1. ከዚህ ቀደም በመንግስት ፖሊሲ ተገቢ ትኩረት ያላገኙ ድሀ የሀብረተሰብ ክፍሎችን (ለምሳሌ፣ በከተማ የሚገኙ ድሃ የሀብረተሰብ ክፍሎች፣ ከብት አርቢዎችን ወዘተ ሊሆን ይችላል) ማሳወቅ
2. የድህነት የተለያዩ ገፅታዎችን ለማሳወቅ
3. አሣዛዊ ያልሆኑ የድህነት አመልካቾች በመለየትና እንደተጨማሪ የድህነት መለኪያ እንዲውሉ በማድረግ
4. አንገብጋቢ የሚባሉ የድህነት ችግሮችን ለይቶ ለማውጣት
5. የድህነት ችግር ዋና ዋና መንስዔዎችን ለይቶ ለማሳወቅ ይገኙበታል።

## ለ. የስትራቴጂው ዓላማዎችንና ግቦችን መወሰን

የድህነት ትንታኔ በማካሄድ በሀገሪቱ ያለው የድህነት መጠንና ዓይነት ከተለየ በኋላ የሚቀጥለው ዋና ተግባር ሰነዱ በስራ በሚውልበት ዘመን በተግባር ለማግኘት የሚፈለጉ ውጤቶችን ለይቶ ማስተቀመጥ ነው። በድቅስ ሰነድ የስትራቴጂው ዓላማዎች ሆነው መቀመጥ ያለባቸው እንዝብጋቢ ትብለው የተለዩ የድህነት ችግርችና ዋና ዋና የድህነት መንስዔ የሆኑ ምክንያቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ጉዳዮች መሆን አለባቸው። እነዚህም ዓላማዎች ህብረተሰቡ የተስማማባቸውና ከመንግስት የማስፈፀም አቅም ጋር የተዛመዱ መሆን ይኖርባቸዋል።

የድቅስ ሰነድ የስራ ዘመን ሶስት ዓመት ነው። በዚህም መሰረት በሰነዱ የሚካተተው ስትራቴጂ ዓላማዎች በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሊሆኑና ውጤቶቹ ሊገኙ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ሆኖም በመጀመሪያ የረዥም ጊዜ ዓላማዎች ተለይተው ሊቀመጡና በነዚህ ላይ የተመሰረቱ የሶስት ዓመት ዓላማዎች ሊቀረፁ ይቻላል።

የድቅስ ሰነድ ዓላማዎች ለይቶ ከማስቀመጥ ተግባር ጋር ተያይዞ የሚከናወነው ሌላው ተግባር በሰነድ የስራ ዘመን ሊደረስባቸው የሚገቡ ግቦችን መጣል ነው። እነዚህ ግቦች በተቀረፁ ዓላማዎች ላይ የሚመሰረቱ ህብረተሰብ የተስማማባቸውና ሀገሪቷ ለስትራቴጂው ተግባራዊነት ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ልታገኝ ከምትችለው የፋይናንስ መጠንና የማስፈጸም አቅም ጋር የተገናዘቡ መሆን አለባቸው።

## ሐ. መንግስት በአሁኑ ወቅት በስራ ያዋላቸው የልማት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች መገምገም

በድህነት ትንታኔ ተለይተው የተቀመጡ እንገብጋቢ የድህነት ችግሮች እነዚህም ለመቀነስ የተቀረፀ ዓላማዎችንና ግቦችን ለማሳካት በአሁኑ ወቅት መንግስት የሚያራምዳቸው ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ምን ያህል ብቁ እንደሆኑ፣ መሻሻል ወይ መለወጥ ያለባቸው ጉዳዮችና ያሉ ክፍተቶች ተለይተው መታወቅ ይኖርባቸዋል።

መንግስት እ.ኤ.አ. በማርች 2001 በዓለም ባንክ በኩል ተቀባይነት ያገኘ ጊዜያዊ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ (PRSP) አዘጋጅቷል። በዚህ ሰነድ መንግስት በሀገሪቱ የሚገኘውን ድህነት ለመቀነስ ያስችላል ብሎ ያመነበትን የፖሊሲ ማዕቀፍ አስቀምጧል። እነዚህም በዋናነት የሚከተሉትን ያካትታሉ፤

- ግብር መር የኢንዱስትሪ ልማት (ADLI)
- የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በቀጣይነት ተግባራዊ ማድረግ
- የፍትህ አስተዳደርና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ
- ያልተማከለ አስተዳደርና ስልጣን ወደ ህዝብ ማውረድ
- አቅም ግንባታ ናቸው

በመሆኑም ነድቅስ ሰነድ ዝግጅት ወቅት በነዚህ የስርራቴጂ ይዘቶች ላይ ህብረተሰቡ በመወያየት ጠቃሚነታቸው ጉድለታቸው እንዲሁም ጠቃሚነታቸው ላይ ግምገማ ማድረግና አጠቃላይ ግንዛቤና ስምምነት ላይ መድረስ ይኖርበታል።

በተለይም የተጠቀሱት የመንግስት ፕሮግራሞች አዲስ ሳይሆኑ ከዚህ ቀደም ለተወሰኑ ዓመታት በተግባር ሲውሉ የቆዩ ስለነበሩ ግምገማው በተጨባጭ በተገኙ ውጤቶች ወይም ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተመስርቶ ሊካሄድ ይችላል። የግምገማው ዓላማ የሚሆነውም መቀጠል ያለባቸውን ለመለየት፤ ችግር ያለባቸውን ቦታዎች ለመለየትና አዳዲስ ፖሊሲዎች ፕሮግራሞችን ለመቅረፅ የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

## መ. ውጤታማ የሆኑ ስትራቴጂዎችላይ ስምምነት መድረስ

ከዚህ በፊት በተዘረዘሩ ተከታታይ ተግባሮች መነሻነት በድቅስ ሰነድ መካተት ያለበትን አጠቃላይ ስትራቴጂና ዝርዝር ፕሮግራሞች መንግስትና ህብረተሰቡ በጋራ በመወያየት ስምምነት ላይ መድረስ የሰነዱ ዋነኛ አብይ ተግባር ነው። የድቅስ ሰነድ አጠቃላይ ሁሉ አቀፍ ይዘት ያለው በመሆኑ በሰነኩ የሚካተተው ስትራቴጂ አጠቃላይ የልማት አቅጣጫን የሚጠቁም በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ

ዘርፎች ትኩረት የሚሰጥባቸውን መስኮች እርስ በርስ የሚኖሩ ቁርኝቶችና መደጋገፎች የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል።

የስትራቴጂው ይዘትም አስቀድሞ ተለይተው በተቀመጡ አንገብጋቢ የድህነት ችግሮችና ዋና ዋና የድህነት መንስዔዎች ላይ በሚገባ የተመሰረተና እነዚህን ችግሮች ለማስወገድና መንስዔዎችን ለመዋጋት በሚያመች መልክ መቀረፅ ይኖርበታል። በዚህ ሂደት የሂደት የሲቪል ማህበራትና ሕዝቡ ባጠቃላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረጉ ከሚታስገኙት ጠቀሜታዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፣

1. መንግስታዊ ካልሆኑ በጎ አድራጊ ድርጅቶች የሚገኙ ጠቃሚና ውጤታማ የሆኑ ልምዶች (በተለይም በጎ አድራጊ ድርጅቶች ነድህነት ዙሪያ ከህብረተሰቡ ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ የረዥም ጊዜ የስራ ልምድ ስላላቸው ከዚህ ቀደም ይጠቀሙባቸው ከነበሩ አሰራሮች ውስጥ ምርጥ የሆኑ ልምዶችን መቅሰም ስለሚቻል)
2. የምርምር ተቋማትና የሙያ ማህበራት ነተስማሩበት የስራ መስክ በልዩ ልዩ ጥናቶች ከሌሎች ሀገሮች ልምዶች የሚቀስሟቸው ጠቃሚ ዕውቀቶችና ግንዛቤዎች ስሚኖሪ በሰነዱ ዝግጅት በሚያደርጉት ተሳትፎ ውጤታማ ስትራቴጂ የመቀየሱ ዕድል የተጠናከረ መሆኑ
3. ሕብረተሰቡ ያመነባቸው ዕርምጃዎች ሰነዱ መከተቱ ሰነዱ የሕብረተሰቡን ድጋፍ እንዲያገኝ ስለሚያደርግ በተግባር በሚውልበት ወቅት ስኬታማነቱ የተጠናከረ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

# ማመሳከሪያ


AFRILINE 2001 "Poverty Reduction Strategies Monitoring Participation"

Berhanu Nega,2001 2001 The PRSP Approach: New elements and their significance"

G Prennushi, 2000 "Indicators for Poverty Reduction Strategies: Good Practice and Suggestions for Ethiopia.

CSPR, 2001 "Progress Report on Civil Society's Participation in PRSPs"

EURODAD 2000: "PRSP Implementation Issues"

Gethaun Tafesse: 2001 "The PRSP Initative: Implications to Ethiopia"

UNDP, 2001 "Lessons from the PRSPs: Perespectives from UNDP"

ODI: 2000 "PRSP Institutionalization Study"

World Bank: 2000 "A new Approach to Country-owned Poverty Reduction Strategies"

________ "Enhanced Initiative for Heavily Indebted Poor Countries Review of implementation"

________,2001 "Poverty Reduction Strategy Source book"

ፌዴራል መንግሥት 1993 የኢትዮጵያ የአጭር ጊዜ የድህነት ማቃለያ ስትራቴጂ (1993-1995)